h) Maysaqarrah xayyoysan waqdi edde xin madqalluk "tembir" xakabah edde haanam faxximta.

## 32) Luulâ taamah eglaali taysaqarre xagoora wagittaama

1 Yayseqerre xagar inki luulâ taamah egla ayseqarre waam timixxigek akah aysaqarre waa sabab essero xayyoyseh kutbeh yaysixxigem faxximta.

2 Ummaan luulâ taamah eglak maysaqarra edde tekke ayrook xabba haanam madqal mannowtam qimbissah.

3 Tayyaaqek matayyaaqa cubbuso tikki itteh, tayyaaqem kee elle xissimta dariifal taamittam xiqtam akah diggoysen luulâ taamah egla wagiita doolat xagaral xayyoowak taysaqarrimeh

4 Rakiibo luulâ taamah eglaali, luulâ taamah yuniyonwa kee luulâ taamah eglaalih federeshinwa faxximta magdooda kibeenim diggoytek geera kulli lon qamalal daqaaral hinnay rasul hinnay magaalah exxal hinnay rakaakayal hinnay federal caddibnal tanih tan luulâ taamah eglaalih baarissoh exxaaxil xayyoowak yaysaqarrimen.

ሸ) ለምዝገባ በሚያቀርብበት ጊዜ ከሚቀርበው መተዳደሪያ ደንቡ ጋር ቴምብር አብሮ መያያዝ ወይም መለጠፍ ይኖርበታል::

## 32. የኅብረት ሥራ ማህበራት መዝጋቢ አካላት

1) መዝጋቢው አካል አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር የማይመዘግበው መሆኑ ሲታወቅ የማይመዘግብበትን ምክንያት ለአመልካቹ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት::

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ከተመዘገበበት ዕለት ጀምሮ ሕጋዊ ህልውናው ይጀምራል::

3) የአዋጭነት ጥናት ተዘጋጅቶ አዋጭ መሆኑ እና በሚደራጅበት አከባቢ መስራት የሚችል መሆኑ የተረጋገጠለት የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ ይመዘገባል::

4) መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት፤ የኅብረት ሥራ ዩኒየኖች እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌደሬሽኖች አስፈላጊውን መስፈርት ማሟላታቸው ሲረጋገጥ እንደየባህሪያቸው በወረዳ ወይም በዞን ወይም ከፍለ ከተማ ወይም በክልል ወይም በፌደራል ደረጃ ባሉ የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል::

5 Namma daqaarih fanal xissimta rakiibo luulâ taamah eglaalih hinnay yuniyonwa rasul hinnay magaalah exxa caddol geytimta luulâ taamah baarissoh xagooral xayyoowak yaysaqarrimen.

6 Namma rasih fanat hinnay magaalah exxah xissimte ummaan luulâ taamah egla rakaakay hinnay magaala xiinissoh caddol geytimta luulâ taamah eglaalih baarissoh xagaral xayyoowak yaysiqirrimen.

7 Baxsa le caalay loonuk ugutak rakaakay caddol yaysaqarrimem xiqewaa kee namma rakaakayih fanat hinnay magaala xiinissoh fanat yan nammey hinnay wohuk biso takke eglaalik xissiimak tamaate ummaan luulâ taamah eglaali federal caddol tan luulâ taamah ejensil xayyoowak taysaqarrime.

8. Luulâ taamah eglaalih liig baaxo caddibnal yaysaqrrime. Baaxo caddol inkih tan luulâ taamah eglaali awlisa luulâ taamah eglaalih liig baaxo caddol yaysaqrrime. Maysaqarrâ sumaqtah warkat keenih yaceen.

5) በሁለት ወረዳዎች መካከል የሚቋቋም መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒየኖች በዞን ወይም ክፍለ ከተማ ደረጃ በሚገኘው የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

6) በሁለት ዞኖች ወይም ክፍለ ከተሞች መካከል የሚቋቋም ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ በሚገኘው የኅብረት ሥራ ማስፋፊያ አካላት ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

7) በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በክልል ደረጃ መመዝገብ የማይችሉና በሁለት ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሚመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚቋቋም ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በፌደራል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ ደረጃ ቀርቦ ይመዘገባል፡፡

8) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሁሉንም የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚወክል የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ይመዘገባል፡፡ ለምዝገባው ማረጋገጫ ህጋዊ ሰርተፊኬት ይሰጠዋል፡፡

9. Luulâ taamah eglaalih liig maysaqarrah xayyoowa waqdi kibeh meqe magdoodak tu

   a) Edde xinti madqa
   b) Aboonu waan taamak 5 liggidih ekraaro
   c) Liig miraacissa amolladi mododul awlisen miroctih migaq kee ferma

10. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 10 elle madqimtennal anuk wagiitah yan doolat xagar eglah kaal xayyowteh tan maysaqarrah assabalta bicsen maysaqarrâ cibtal yaceeh. Yaysaqarre xagar yismiteh yan edde xin madqak inki korraq yeyseqerren luulâ taamah eglah yaceen.

11. Kulli luulâ taamah eglak rakiiboh alhum wagiita doolat xagar bicsa cibtal kobxisak yaysaqarreeh dagnal kulli 3 liggidal yaqusbuseenim faxximta.

12. Ummaan luulâ taamah eglaali kulli caddol xissiimak faxximta magdooda kiban waqdi maytanih madqa numiinoh xagarih diggoosih sumaq warkat keenih yantocowwe.

13. Luulâ taamah eglaalih yaceen sumaq warkat elle faxxiiminnaan innal sitta ceelam bictaah baxsa lem bicta. Baxaabaxsa le addatino lem bictah.

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ ለምዝገባ ሲቀርብ ማሟላት የሚገባው መስፈርቶች መካከል፤

   ሀ) የመተዳደሪያ ደንብ፣
   ለ) ስለሚከናወናቸው ጉዳዮች የያዘ የ5 አመት የስትራቴጂክ እቅድ፣
   ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሊግ የሚመሩ ከሊጉ ጠቅላላ ጉባኤ የተወከሉ አመራሮች ስምና ፍርማ፣

10) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለስልጣን በኅብረት ሥራ ማህበሩ የቀረበለትን የምዝገባ ማመልከቻ በተዘጋጀው የምዝገባ ቅጽ ወይም ፎርማት መሰረት መተዳደሪያ ደንብ እና የንግድ ስራ እቅድ በመመዝገብ የምስከር ወረቀት ይሰጣል:: በመዝጋቢው አካል የተረጋገጠ የመተዳደሪያ ደንቡን 1 ኮፒ ለተመዝጋቢው ኅብረት ሥራ ማህበር ይሰጠል::

11) የማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር መሰረታዊ መረጃ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው ቅጽ ወይም ፎርማት ተሰብስቦ በመዝገብ ላይ ቢያንስ በየሦስት አመቱ መታደስ ይኖርበታል::

12) የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው ተደራጅተው አስፈላጊውን መስፈርት ሲያሟሉ ቋም የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስከር ወረቀት ይሰጣቸዋል::

13) ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጠው የምስከር ወረቀት እንዳስፈላጊነቱ ተመሳሳይ ወይም የተለያየ መልክ እና ይዘት ሊኖረው ይችላል::

Qafar Ag/Ra/Do Qafar Afaay Qaadaa Kee Adar Kusaagih Fante
Afar National Regional ... Afar Language Cult... History Research Center

14. Luulâ taamah eglaali yaysaqarre ummaan num yaysaqarruh kaal xayyowte sanadwak ugutak, elle yaysaqarre "chek list" bicsam faxximta.

15. Aysaqorri sumaq yaceenik afat aysoqarri mihrat li xissimte eglah addal amoh geytimak "chek listik ugutak kusaaqisam faxximta.

16. Luulâ taamah eglaali xisa maraa kee yaysaqarre mihrat li sittallih gacak luulah eglaali xiqto lek waytam diggoysan

17. Bicsen "chek list" ugutak yaysaqarrimoonuh dudda loonum diggoysan waqdi maysaqarrah sumaq keenih yaceenim faxximta.

## 33. Maysaqarrâ sumaaqih warkat wagittaama

1 Ummaan luulâ taamah eglaali xissiimak taamat culaanak afal kukti ixximak 985/2009 elle iyya innal wagiita doolat xagarak maysaqarrâ sumaq warkat geyanam faxximta

2 Ummaan qusubih xissimta luulâ taamah egla amolladi mododul dooren taama miraacissa maroh adoytiitih gitaak maysaqarrah faxximta magdooda kibak madqâ numiinoh asmat keenih yacoonuh wagiita doolat xagaral essero xayyoysan

14) የኅብረት ሥራ ማህራትን የሚመዘግብ ማንኛውም መዝጋቢ ባለሙያ ለምዝገባ የቀረቡለትን ሠነዶችን መሠረት በማድረግ የሚመዝንበትን ቼክሊስት ማዘጋጀት አለበት፣

15) የምዝገባ ሠርተፊኬት ከመስጠቱ በፊት ማንኛውም መዝጋቢ አካል ለመደራጀት የቀረበውን የኅብረት ሥራ ማህበር በአካል በመገኘት በተዘጋጀው ቼክሊስት መሰረት መገምገምና መመዘን ይኖርበታል።

16) የኅብረት ሥራ ማህራትን የሚያደራጀው እና መዝጋው ባለሙያዎች ለምዝገባ ብቁ የሚያደርጋቸውን ግምገማ እና ምዘና በመቀናጀት ያካሄዳሉ።

17) በተዘጋጀው የምዝገባ ማረጋገጫ ቼክሊስቱ መሰረት ለምዝገባ ብቁ መሆናቸው ሲረጋገጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት መስጠት አለበት።

## 33. ስለ የምዝገባ የምስክር ወረቀት

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ተደራጅተው ወደ ስራ ከመግባታቸው አስቀድሞ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 ዓ.ም በተደነገገው መሰረት አግባብ ካለው ባለስልጣን የምዝገባ ሰርተፊኬት ማግኘት አለባቸው።

2) ማንኛውም በአዲስ የተደራጀ የኅበት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ አባላት በተመረጡ የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት አማካይነት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ መስፈርቶችን በማሟላት የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ እንዲሰጣቸው አግባብ ላለው ባለስልጣን ጥያቄ ያቀርባሉ።

3 Ummaan sittalluk xissiimak taamituh bicsite num hinnay eglat akah xissiimen madma arac xagsoonuh kee madqâ focal amaxxag yaalluh wagiita doolat xagarak madqal mamaxxaga le xagar kinniimih diggoosih sumaq warkat geyam faxximta.

4 Ummaan luulâ taamah egla taysaqarrimuh faxximta magdooda kibak wagiita doolat xagar taysaqarrimu idini teetih yeceek maytanih madqal yimixxige xagarih sumaq warkat geytam faxximte.

5 Ta maasayyak ugutak xissimte ummaan luulâ taamah egla taysaqarrimuh faxximta magdooda kibbimtek aysaqorri sumaqih warkat teetih yaceen.

6 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak985/2009 maasayyak (11) nali maasayyak (1 kee 2) madqimtem elle anuk ummaan luulâ taamah egla madqâ nummiinoh diggoosih sumaq warkat taamah aracal hinnay kutbe buxal akak yambulle aracal daffeysan.

## 34. Elle sugah yaceen maysaqarrâ sumaq warkatih acwa

1 Luulâ taamah eglaali kulli caddol xissiimak faxximta magdooda kibe weenik inki liggidah dibuk suga elle sugáh madqa numiinoh diggoosih sumaq warkat keenih yaceen.

3) ማንኛውም በጋራ ተደራጅቶ ለመስራት የተዘጋጀ ግለሰብ ወይም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚቋቋምበትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲችልና በህግ ፊት ተቀባይነት እንዲኖረው አግባብ ባለው ባለስልጣን ተመዝግቦ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት::

4) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ መስፈርቶችን አስቀድሞ በሚሟላት አግባብ ባለው ባለስልጣን ለመመዝገብ ከተፈቀደለት ቋሚ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት::

5) በዚህ አንቀጽ መሠረት ለሚደራጅ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ መስፈርቱን ሲያሟላ የምዝገባ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል::

6) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ (1 እና 2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በሥራ ቦታ ወይም ጽ/ቤት ውስጥ ግልፅ በሆነ ቦታ እንዲታይ ሆኖ መቀመጥ አለበት::

## 34. ጊዜያዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በየደረጃው ተደራጅተው አስፈላጊውን መስፈርት ካላሟሉ ለአንድ አመት ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል::

2 Elle sugâ warkat geyte luulâ taamah egla too uddurih addat ummaan luulâ taamah egla le gar kee dirki lon.

3 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 10 nali maasayyak 8 madqimtem elle anuk sagla alsih addat deedalta magdooda kibak maytanih sumaq warkat herge weenik ossotinah 3 alsih ekeka teetih yaceenim bictah.

4 Teetih yeceen uddurut deedalta magdooda kibak faxximta mekla abba hayteh maytanik sumaq warkat geyan waqdi luk sugen elle suga sumaq warkat gacsaanah.

5 Ta maasayyak ugutak elle suga sumaq geyte egla inki liggidih addat faxximta kibbi hayteh maytani sumaq hirge wayte egla inki liggidaak geera madqa focal hirgo mali. Wagiita doolat xagar egla iggilli heeh mano akah aalle wayta innah abele.

6 Kukti ixximak 985/2009 maasayyak 10 nali maasayyak 2(a-g) madqimtem elle anuk ta maasayyak 33 nali maasayyak 3(a-h) ugutak maysaqarrah xayyowte magdoodi inkih kibe wayte luulah eglah wagiitah yan doolat xagar inki liggidak biso taamitewaa elle suga sumaq warkat acayuk raqte magdooda yeceen uddurut kibaanam faxximta

2) ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ሥራ ማህበር በተመዘገበበት የጊዜ ገደብ ውስጥ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ያለው መብት እና ግዴታ ይኖረዋል፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 10 (8) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዘጠኝ ወራት ውስጥ የተጓደሉትን መስፈርቶችን አሟልቶ ቋሚ የምስክር ወረቀት ካልወሰደ ተጨማሪ 3 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ሊሰጠው ይችላል፡፡

4) በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ የተጓደሉትን መስፈርቶች ካሟላ ተገቢውን ክፍያ ፈጽሞ የቋሚነት የምስክር ወረቀት በማግኘት ነባሩን ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

5) በዚህ አንቀጽመሠረት የጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያገኘ ኅብረት ስራ ማህበር በአንድ ዓመት ውስጥ ተፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ በቋሚነት ካልተመዘገበ ከአንድ አመት በኋላ በህግ ፊት ተቀባይነት አይኖርም፡፡ አግባብ ባለው ባለሥልጣን የኅብረት ሥራ ማህበሩን በማፍረስ ህልውናውን እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

6) በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 10 ንኡስ አንቀጽ 2 /ሀ/ እስከ /ሰ/ የተደነገገው እንደጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 33 ን/አንቀጽ 3 ከ (ሀ-ቀ) መሰረት ለምዝገባ የቀረቡትን መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ያላሟላ ኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ያለው ባለስልጣን ከአንድ ዓመት በላይ ላልበለጠ ጊዜ የሚያገለግል ጊዜያዊ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በመስጠት የተቀሩትን መስፈርቶች በተሰጠው የጊዜ ገደብ ማማሟላት አለበት፡፡

## 35) Badali maysaqarrah sumaaqih warkatih acwa

1 Luulâ taamah eglaali badali maysaqarrah sumaaqih essero baahaanam warkat keenik bayek, hinnay yoomek hinnay migaq korseenik takke waqdi tonna kinnuk kibeh meqem ciggiltaama

a) Luulâ taamah egla maysaqarra sumaaqih warkat teetik bayek malcina ayroh addat wagiita doolat xagarah warsan. Akah warsen xagar cubbusak yismiteek geera badali sumaq warkat faaticissi heeh namma ayroh addat yacee.

b) Madqa numiinoh digoosih sumaq warkat yoome kaa tekkek sumaq warkat yoomem wagiita doolat xagar diggoysek namma ayroh addat badali sumaq warkat yacee.

c) Ummaan luulah egla amolladi mododul baxsa le edde cabol faaticisen migaq korsih essero xayyossek wagiita doolat xagar maybalaalaqal edde tewqe 30 ayroh addal sadi amaate week migaq korsa faaticisak badalih sumaq warkat namma ayroh addat aceele.

d) Badali sumaq warkatih essero wagiita doolat xagar cayse waytek wagiita doolat xagar namma ayroh addat badali akah aceewaa sabab qaddoysak kutbeh luulâ taamah eglah ruubak yaysixxige.

## 35. ምትክ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1) ኅብረት ሥራ ማህበራት ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ጥያቄ የሚቀርበው የምስክር ወረቀቱ ሲጠፋ ወይም ሲበላሽ ወይም የስም ለውጥ የሚደረገው ሆኖ የሚከተሉት ተሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡

ሀ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ሲጠፋበት በሰባት ተከታታይ ቀናት ውስጥ አግባብ ላለው ባለስልጣን ሲያሳውቅ አግባብ ያለው ባለሥልጣን በህግ አካል የተረጋገጠ መረጃ መቅረቡን አጣርቶ ምትክ የምዝገባ መስከር ወረቀቱን አጽድቆ በሁለት ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ ይሰጣል፡፡

ለ) የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸውን የምስክር ወረቀት አግባብ ያለው ባለስልጣን ሲያረጋግጥ፣ ከሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ይሰጣል፡፡

ሐ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በጠቅላላ ጉባኤ ልዩ ውሳኔ የፀደቀ የስም ለውጥ ጥያቄ ሲያቀርብ አግባብ ያለው ባለሥልጣን አጣርቶ ሰፊ ሽፋን ባለው ጋዜጣ ያወጣል፡፡ ጋዜጣው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር ሰላሰ ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ የስም ለውጡን አጽድቆ ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በሁለት ተከታታይ የስራ ቀን ውስጥ ይሰጣል፡፡

መ) ምትክ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ለመስጠት የቀረበው ጥያቄ አሳማኝ ካልሆነ አግባብ ያለው ባለስልጣን ከሁለት ተከታታይ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ የማይሰጥበትን ምክንያት በመግለጽ በጽሑፍ ለኅብረት ስራ ማህበሩ ያሳውቃል፡፡

## 36) Caddibnak ugut aba maysaqarrâ sumaaqih acwa wagittaama

1 Yaysaqarrimuh tamaate ummaan luulâ taamah egla bicseenih yan magdok ugutak agdaabe caddo teetek taybulle sissin bisu le sumaq warkat teetih yaceen.

2 Luulâ taamah eglaali taamah agdaabel yuybulleen xaluk ugutak ciggiila bisle sumaq warkoota keenih aceelon.

- a) Caddibnak "A" baxsima mari "anxaxin" bisule sumaqta
- b) Caddibnak "B" baxsima mari "walqinaan" bisu le sumaqta
- c) Caddibnak "C" baxsima mari "qisi" bisule sumaqta geelon.

3 Keenih yaceenih yanin sumaaqak ugutak ken caddibna ceela tuxiq kee xoqoysi hinnay qokol kummuqta geelon.

4 Ansaxin sumaq warkat geyta luulâ taamah eglaali

- a) Akah xissiimen madma abinal kaxxa caddol yugdube mara
- b) Adoytit kaxxa caddol xoqoysi leela abe mara
- c) Adoytiitik rakiibok yan maddur kee ayyuntiinô ceyaayi yifgide mara

## 36. ደረጃን መሰረት ያደረገ የምዝገባ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

1) ለምዝገባ የሚቀርብ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በተዘጋጀው የመመዘኛ መስፈርት መሰረት የአፈጻጸም ደረጃቸውን የሚገልጽ የተለያየ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል::

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያገኙት የምስክር ወረቀት እንዳስመዘገቡት ውጤት ዓይነት የሚከተሉትን ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ሊሆን ይችላል:-

ሀ) በደረጃ "ሀ" የሚለዩት "አረንጓዴ" ቀለም መልክ ያለው የምስክር ወረቀት፣

ለ) በደረጃ "ለ" የሚለዩት "ቢጫ" ቀለም መልክ ያለው የምስክር ወረቀት፣

ሐ) በደረጃ "ሐ" የሚለዩት ደግሞ "ቀይ" ቀለም ያለው ላይ የምስክር ወረቀት፣

3) በሚሰጣቸው የምስክር ወረቀት መሰረት ደረጃቸውን የሚመጥን ጥቅማ ጥቅምና የድጋፍ ፓኬጅ የሚያገኙ ይሆናል::

4) የአረንጓዴ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚያገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት፤

ሀ) የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማና ተግባር በላቀ ደረጃ ያሳኩ፣

ለ) አባላትን በከፍተኛ ደረጃ ተጠቃሚ ማድረግ የቻለ፣

ሐ) የአባላትን መሰረታዊ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ እና ማሕበራዊ ችግሮቻቸውን የፈቱ፣

d) Dariifâ daddoos kee dadalat gaba asgalluk ummattah ugxeexa sahayloyse mara

e) Doolat daffesse maddur kee ayyuntiino maadima gufoonuh giffo le gaba gacse mara

f) Adoytit fanat meqe angaaraw kee ogoysol sittallih taamitoonuh meqe niya yaybullee mara

5 Walqin bisu le sumaqta akah yaceenim akah xissiimen madma ta maasayyak 36 nali maasayyak 4(a-f) rooriseenimik garab yugdube mara.

6 Ta maasayyak 36 nali maasayyak 5 elle warsen innal namma udduruy sittalakleh yanih iyya aysiise weeh rammale walqinaanak mallaytal yeedee mari ciggiilak ramma le qisi fan ken oobisan.

7 Akah xissimen rakiibo madma duuduse wee mari (eglaali) qasa bisu le sumaq warkat keenih yaceen.

8 Namma adda sittallakleh aysiise kal geytimta luulâ taamah egla kulli caddol tan wagiita doolat xagar kusaaqisak cubbusak tet yaggilem hinnay tet yasgallemih edde cabo tatrusam duudah.

9. Ta maasayyak 36 nali maasayyak 8 madqimtem elle anuk qasa bisule sumaq warkat akah yaceen eglaalik diglo hinnay asgolli edde cabo tatrusaanam:

መ) በአካባቢ ልማት እና ዕድገት ላይ ባደረጉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሕብረተሰቡን ችግሮች በከፍተኛ ደረጃ ያቃለሉ፣

ሠ) መንግስት ላስቀመጣቸው የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ግቦች ስኬት የድርሻቸውን በከፍተኛ ደረጃ በመወጣት ላይ ያሉ፣

ረ) ከአባላቱ ያለው የጋራ ግንኙነትና ትስስር እና አባላቱ አብረው ለመስራት የሚያሳዩት የተጠናከረ ቁርጠኝነት ያላቸው፣

5) ብጫ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማ በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 4 (ሀ-ረ) በተገለፀው መሰረት በመካከለኛ ደረጃ ያሳኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 5 በተገለፀው መሰረት ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሳይሻሻል ከዝቅተኛው የቢጫ ጫፍ ላይ የቆየ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚቀጥለው ወደ ቀይ ዝቅ ይደረጋል፣

7) የተቋቋሙበትን መሠረታዊ ዓላማ ማሳካት ያልቻሉ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

8) ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት ከሁለት ተከታታይ ጊዜ በላይ ሳይሻሻል ይዘው የሚገኝ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በየደረጃው የሚገኘው አግባብ ያለው ባለስልጣና ጥናት ላይ በመመስራት የማፍረስ ወይም የማዋሃድ ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

9) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 36 ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀይ ቀለም ያለው የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት የማፍረስ ወይም የማዋሃድ ውሳኔ የሚተላለፈው፤

a) Daffeysen magdoodik ugutak luulâ taamah egla taama bagul anewaytam timixxigek
b) Diglo siirat katayak agile kal isih tiddigilek
c) Akah xissiimen madmah bagul ane waanam diggoytek
d) Adoytiitih uli xoqoysii kee ayfaafay acee waam timixxigek
e) Agdaabe teetik yaysiiseenimih caddot ane waytek
f) Maqarroysoonuh uli doorit ane week
g) Adoytiitit uli angaaraw aalle waam diggoytek
h) Taama miraacissa maroh adoytit taama bagul ane week.

## 37) Aysaqorri sumaq warkatih aqasbusiyya

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 147/91 ugutak xissimte eglaali ta miraacsenta tewqeemiik xabba heenih inki liggidih addat kukti ixximak 985/2009 maasayyak 20 nali maasayyak(1) ugutak aysaqorra yaqusbuseenim keenil tan.
2. Ta maasayyak 37 nali maasayyak(1) madqimtem elle anuk luulâ taamah eglaalih yeceen maysaqarrâ sumaqta kulli sidiica liggidal yaqusbuseenih.

ሀ) ከተቀመጠው መስፈርት መሰረት የኅብረት ሥራ ማህበሩ በስራ ላይ የሌለ መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ለ) የማፍረስ ሕግን ተከትሎ ያልፈረሰ ግን በራሱ የፈረሰ፣

ሐ) በተቋቋመበት አላማና ተግባር ላይ አለመኖሩ ሲረጋገጥ፣

መ) ለአባላት ምንም ዓይነት የኢኮኖሚ ጠቀሜታ እና አገልግሎት የማይሰጥ ሲሆን፣

ሠ) አፈፃፀሙን ለማሻሻል የማይቻል ደረጃ ላይ ሲገኝ፣

ረ) ለማጠናከር ምንም አማራጭ ሁኔታ ሳይኖር ሲቀር፣

ሰ) ከአባላት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሸ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አካላት በሥራ ላይ ከሌሉ፣

## 37. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለማሳደስ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር147/91 መሠረት የተደራጀ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ይህ የአደረጃጀት መመሪያ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ በ1 አመት ጊዜ ውስጥ በአዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ምዝገባቸውን ማሳደስ ይኖርባቸዋል፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 37 ንኡስ አንቀጽ (1) ስለ ምዝገባ የምስክር ወረቀት እድሳት የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለኅብረት ሥራ ማህበራት የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት በየሶስት ዓመቱ ይታደሳል፡፡

3.Ta maasayyak 37 nali maasayyak (2) madqeenim elle anuk maytanih yeceen sumaq warkat ukummook geera hinnay sumaq warkat yuqusbuseeniik wadir sidiica liggidak biso ma taamita (ma yanfiqa)

4. taysaqorri sumaq warkatih uddur gaba kaluh inki alsi raaqa waqdi wagiita doolat xagaral xayyoowak warkat yaqusbuseenim faxximta.

5. Ta uddurih addat aqusbuse ween sumaqtah amol tan luulâ taamah eglaali madqal hirgo malon. Tonna kinnuk wagiita dagaral xayyoowak sumaq warkat yaqusbuseenim faxximta.

6. Ummaana luulâ taamah egla maysaqarrâ sumaq taqusbusuh ciggiltam kibbimtam faxximta.

a) Luulâ taamah egla yiysiisen edde xintak 3 korraq
b) 3 liggidih makcagur ekraaro
c) Luulâ taamah eglak amolladi ceelo qaddossa ux 3 liggidih gabbaaqu (aybalalaaq cibta xaksb tan)
d) Amolladi mododul faaticisen ooxit gabbaaqu, addat tirfii kee kasaara gaddaa kee abud maybalaalaqa, korraq
e) Eglak caddibna, xiqtô mamaxxagah diggoosih sumaqta
f) Ciggiila 3 liggiidih ekraaro. (3 liggidih ekraaroh cibta xakabah tan)
g) Aqusbusiyyi meklah yoofenta xayyoysaanama.
h) Adoytit mangah ascossa (alhum) le sanada

3) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቋሚ የምስክር ወረቀት የአገልግሎት ዘመን ከምስረታ በኋላ ወይም የምስክር ወረቀቱ ከታደሰ ከሦስት ዓመት በላይ አያገለግልም፡፡

4) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የአገልግሎት ጊዜ ከማብቃቱ ከአንድ ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በየደረጃው ለሚገኘው አግባብ ላለው ባለስልጣን ቀርቦ መታደስ አለበት፡፡

5) በዚህ የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ የማይታደስ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ሕጋዊ የምስክር ወረቀቱን በሕግ ዘንድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለሆንም አግባብ ባለው ባለስልጣን ሕግን ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ሊነጥቅ ይችላል፡፡

6) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚከተሉትን መሟላት አለበት፡፡

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የተሻሻለ የመተዳደሪያ ደንብ ሦስት ቅጂ፣
ለ) የሦስት አመት ስትራቴጂክ እቅድ፣
ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን አጠቃላይ አቋም የሚገልፅ ያለፉት ሦስት አመታት አጭር የጽሁፍ መግለጫ፤ መግለጫው በአዝል ውስጥ ተመላክቷል፡፡
መ) በጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀ የዘመኑ ከኦዲት ሪፖርቱ ውስጥ የትርፍና ኪሳራ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ የተመሳከረ ኮፒ፣
ሠ) የብቃት ደረጃ ዕውቅና ማረጋገጫ ሠርተፊኬት፣
ረ) የቀጣይ ሦስት ዓመት ዕቅድ፣ የሦስት አመቱ አቅድ ፎርማቱ በአዝል ውስጥ ተመላክቷል፡፡
ሰ) ለዕድሳት የሚከፈለውን ገንዘብ ገቢ ያደረገበት ደረሰኝ፣
ሸ) የአባላትን ቁጥር የሚገልፅ መረጃ፣

Qafar Ag/Ra/Do Qafar

i) Tatre 3 liggidak sittalakleh kasaara abeweenimih alhumu

j) Tatre 3 liggidah adoytiitik qadaaga asgolli fantiital fayya iyyem taybulle alhum

ቀ) በተከታታይ ላለፉት ሦስት አመታት ኪሳራ ያላሳየ ስለመሆኑ የሚያሳይ መረጃ፣

በ) ባላፉት ሦስት አመታት በአማካይ የአባላት የግብይት ተሳትፎ የተሻሻለ መሆኑን የሚሳይ መረጃ፣

7. Ta maasayyak 37 nali maasayyak (6) ugutak aysaqorri sumaq warkat aqusbuse wayte luulâ taamah eglal wagiita doolat xagarih xaquuk ciggilta maaqattooti beelon:

a) Doolatak geyak sugen catoota aggiriqqele

b) Aysaqorri sumaqtah bagul akkuk sugte ambalaalitte angaddaabe mageyta.

c) Wagiitah yan doolat xagar ken sumaqta moddoqiinu malim rettimat ham (yaysixxigem) bictah.

7) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት ያላሳደሰ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለሥልጣን የሚከተሉት እርምጃዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፤

ሀ) ከመንግስት የሚያገኛቸውን ማናቸውም ድጋፎች ይቋረጣሉ፣

ለ) በምዝገባ ምስክር ወረቀቱ የሚያደርጋቸው ማናቸውም ውሎች እና ስምምነቶች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

ሐ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የምዝገባ ምስክር ወረቀቱ ህጋዊነት የሌለው መሆኑን የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ሊያሳውቅ ይችላል፣

8. Ta maasayyak 37 nali maasayyak (7)(a-c) madqimtem elle anuk, maaqatta katayak sumaq warkat yaqusbusem faxe wayte egla faxe ikkel oggol mali. Wagiitah yan xagar madqa elle itta innal sumaq warkat akah gacsan innah aba.

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 37 ንዑስ አንቀፅ 7 (ከሀ-ሐ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ እርምጃ ተከትሎ የምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ አግባብ ያለው ባለስልጣን ሕግን ተከትሎ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን እንዲመልስ ያደርጋል፡፡

9. Luulâ taamah eglaalih xisoh miracsentak ugutak wagiita doolat xagar raagte luulâ taamah eglaali qagitak elle yaysaqarrimen innaa kee uddur rettimat haak, kutbeh yaysixxigem faxximta.

10 Wagiita doolat xagar daffeyse abni magdok ugutak aysaqorri sumaq warkat qagitak yaqusbusoonuh:

   a) Sissin rettimaamit xoqoysimak seeco tatrusa
   b) Seeco hinnay warkat gufeh yan luulâ taamah egla xayyoowak sumaq warkat taqusbusem faxximta.
   c) Eglak taama miraacissa maroh gitaak aqusbusiyyi essero kutbeh xayyowtam faxximta.

1 Wagiita doolat xagar aysaqorri sumaqta yaqusbusuh 3 adoyta le maro xisa

## 38) Taqusbuse marok taamaa kee qaaqa

1 Luulâ taamah eglah cisab fokkaaqeenik waytam diggossa

2 Eglaalik amolladi gaddaa kee abud maybalaalaqa luglugo luk xayyowtek waytam yasmiten.

3 Eglah adoytiitih oyti luglugo luk xayyoowek waytam

9) የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት መመሪያ መሰረት በማድረግ አግባብ ያለው ባለስልጣን ለነባር የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደገና ስለሚመዘገብበት ሁኔታና የጊዜ ገደብ በሚዲያ ወይም በጽሁፍ መሳወቅ ኖርበታል።

10) አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚያስቀምጠው አሰራር መስፈርት መሰረት የምዝገባ ሠርተፊኬት እንደገና ስለማደስ፤

   ሀ) የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ጥሪ ያስተላልፋል፣
   ለ) ጥሪ ወይም ደብዳቤ የደረሰው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቀርቦ ሠርተፊኬቱን ማሳደስ ይኖርበታል፣
   ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አማካኝነት የእድሳት ጥያቄ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፣

11) አግባብ ላለው ባለስልጣን የምዝገባ ሠርተፊኬት ለማሳደስ የሚሰሩ 3 አባላት ያሉት የእድሳት ኮሚቴ ያቋቁማል።

## 38. የእድሳት ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ መመርመሩን ያረጋግጣል፣

2) እድሳት የሚደርጉ የኅብረት ሥራ ማህበራትን አጠቃላይ የሀብትና እዳ መግለጫ መረጃ ተጣርቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፤

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት መረጃ ተጣርቶ መቅረቡን ያረጋግጣል፣

4 Eglak tangayye ikoo kee maytanih ikoh oyti xayyoowek waytam digoysan yaysaqerren

5 Eglak edde xinti madqa qusba gurral bicseenik waytam diggoysan

6 Eglah cato yakke taamah ekraaroh qagunti bicseenik waytam diggoysan.

## 39) Aysaqorri sumaaqih warkat geyoonuh takke mekla

1 Ummaan luulâ taamah egla maysaqarrah xayyowta waqdi, kukti ixximak 985/2009 kee tet yagdaboonuh tewqe madqak ugutak maysaqarrah meklan maali ciggiltam addat le

a) Qusubih xissimta luulâ taamah eglah maytanih aysaqorrah sumaqta geyoonuh 100 birri

b) Badal sumaqta geyoonuh 200 birri

c) Elle sugah aysaqorri sumaqta faxa marah 50 birri

d) Aysaqorri sumaqtah aqusbusiyyah 100 birri

2 Ummaan luulâ taamah egla issi migaaqal banki culussay, woo yoofenta xakbisak xayyoowaama.

## 40) Aysaqorri sumaq warkat elle waasima gurra

1 Ummaan luulâ taamah egla ciggilta caalootal aysaqorrak waasimtah.

4) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶችን መረጃ መቅረቡን ያረጋግጣል፣ ይመዘግባል፤

5) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ በአዲስ መልኩ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤

6) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያግዙ ረቂቅ የሥራ እቅድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል፤

## 39. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ስለሚደረግ ክፍያ

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለምዝገባ በሚቀርብበት ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 እና ለማስፈጸም በወጣው ደንብ መሰረት ሆኖ የምከፈለው የምዝገባ ክፍያ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

ሀ) በአዲስ ለሚደራጅ የኅብረት ሥራ ማህበር ቋሚ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 100.00

ለ) ምትክ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 200.00

ሐ) ጊዜያዊ የምዝገባ ሠርተፍኬት ለማግኘት ብር 50.00

መ) ለምዝገባ ሠርተፍኬት ዕድሳት ብር 100.00

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በስሙ በባንክ ገቢ የሆነበትን ደረሰኝ አንድ ኮፒ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

## 40. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ስለሚከለከልበት ሁኔታ

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በሚከተሉት ምክንያቶች ምዝገባ ይከለከላል፡

a) Dariifal teetik duma too migaq kee astal teyseqerrime egla tanim diggoytek
b) Luulah egla issi cogaysoh cubbuso aalle waytek
c) Madma teetik kukti ixximak 985/2009 hinnay wagiita doolat xagar yeyyeeqe miracsental saduh tanim tekkek maysaqarra sumaq warkat mayantocowwima.

## 41) Aysaqorri sumaaqih warkatat haan solo wagittaama

1 Ta maasayyak ugutak xissimte luulah egla kukti ixximak 985/2009 ugutak xissiime waytem wagiita xagar diggoysek yeceen warkatat solo ham duudah hinnay bukkusam xiqah. Takkay immay warkat akah yayseede hinnay bukkusa sabab amolladi mododuh yaysixxigeh.

2 Maysaqarrâ sumaq warkat akah yeceen ummaan luulâ taamah egla kukti ixximak 985/2009 ugutak ciggilta sababitteh solsimtam xiqtah.

a) Tewqeh tan kuktitte, madqooqii kee miracsentitte assakaxxe weenik
b) Adoytit gar kee xoqoysi hinnay baaxo maddur biyaktam baaheenik
c) Doolat radmot bice wayteeh, solo faatica edde gaetek

ሀ) በአከባቢው አስቀድሞ በተመሳሳይ ስምና አርማ የተመዘገበ ኅብረት ሥራ ማህበር ያለ መሆኑ ከተረጋገጠ፤

ለ) እንደ አስፈላጊነቱ የራሱ የሆነ የፕሮጀክት ጥናት የሌለው ከሆነ፤

ሐ) በአዋጅ ቁጥር 985/2009 እና በዚህ አንቀጽመሰረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ያላሟላ ከሆነ፤ ዓላማው የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 ወይም አግባብ ባለው ባስልጣን የወጡ መመሪያዎችን የሚጻረር ከሆነ ተመዝግቦ የምስክር ወረቀት ማግኘት አይችልም፡፡

## 41. የምዝገባ የምስክር ወረቀትን ስለማገድ

1) በዚህ አንቀጽመሠረት የተመዘገበ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር በአዋጅ 985/2009 መሠረት አለመስራቱን አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲረጋገጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ሊያግድ ወይም ሊነጥቅ ይችላል፡፡ ሆኖም የምስክር ወረቀት በምን ምክንያት እንደሚያግድና እንደሚነጥቅ ለጠቅላላ ጉባዔ ያሳውቃል፡፡

2) የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በአዋጅ ቁጥር 985/2009 መሰረት በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ከስራ ይታገዳል፡-

ሀ) ቀደም ሲል ያቀረባቸው የመመዘኛ መስፈርቶች የተጭበረበሩ ወይም ያልተሟሉ መሆኑን በክትትል እና ማምገማ ወቅት ከተረጋገጠ፤
ለ) የሚጠበቅበትን ትክክለኛ የሆነ መረጃ ለመዝጋቢ አካላት ያላቀረበ ከሆነ፤
ሐ) የወጡ አዋጆች፤ ደንቦች እና መመሪያዎችን አክብሮ የማይገኝ ከሆነ፤

d) Adoytit gar kee xoqoysi hinnay baaxo maddur biyaktam baaheenik

መ) በአባላት መብትና ጥቅም ላይ ወይም በአገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርስ መሆኑ ተረጋግጦ ሲቀርብ፣

e) Doolat radmot bice wayteeh, solo faatica edde gactek

ሠ) መንግስት ፖሊሲ ጋር የማይጣጣም ሲሆንና እንዲታገድ ሲወሰን፣

f) Ceela qokol geyah aqusbusiyyi uddur tatrusek hinnay dirki kibe waytek

ረ) ተገቢው ድጋፍ እየተደረገለት የእድሳት ጊዜውን ያሳለፈ ወይም የሚጠበቅበትን ግዴታ ያልተወጣ፣

3 Ta maasayyak 41 nali maasayyak (2)(a-f) elle madqen gurral tekke soolisiyyak waqa le luulâ taamah egla, solo nek ugusa axcuk inki alsih addat wagiita xagarah xayyoysaama. Weeqa waktil xayyoowe waytek wagiita xagar inkih tet duugaamih gexsot culam bictah.

3) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 41 ንዑስ አንቀጽ 2 ከ(ሀ-ረ) በተደነገገው መሰረት በእግዱ ላይ ቅሬታ ያለው የኅብረት ሥራ ማህበር እግዱ እንዲነሳለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን አግባብ ላለው ባለስልጣን ማቅረብ ይርበታል። እግዱ እንዲነሳለት በወቅቱ ካላቀረበ አግባብ ያለው ባለስልጣን የመሰረዝ ሂደቱ ይጀመራል፤

4 Luulâ taamah eglat tumbulleeh tan boolaali massossah gide teetih ma qambaalan. Sumaq warkat soolot yan waqdi abba haan ambalaalitte inkih oggol mali.

4) ኅብረት ሥራ ማህበሩ የታዩበት ጉድለቶች እስኪስተካከሉ ድረስ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ አገልግሎት ሊሰጥ አይችልም። በዚህን ጊዜ በምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በመጠቀም የሚደረጉ ማናቸውም ውሎች እና አሰራሮች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።

5 Wagiitah yan doolat xagar sumaq warkat macah soolisem kee eglak tumbullee raaqitte qaddoysak 15 ayroh addat solo edde gacteh tan eglah kutbel yaysixxigem faxximta.

5) አግባብ ያለው ባልስልጣን የምዝገባ የምስክር ወረቀቱ በምን ምክንያት እንደታገደ እና የታዩ ጉድለቶችን በመግለጽ በ15 ቀናት ውስጥ ዕገዳ ለተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር በደብዳቤ ማሳወቅ ይኖርበታል።

6 Soolo edde heen luulah egla, solo akah gacteemih sabab qaddossa warkat tet gufe ayrook xabba haanam inki alsih addat tumbulle boola massossam taysixxigem faxximta.

## 42) Sumaq warkat maysaqarrak duugaanam wagittaama

1 Umman luulâ taamah eglah sumaqta ciggilta sababitteh maysaqarrak duugumtam xiqtah

a) Luulah egla sumaq elle geytem duquurusenta tekkek, dirab alhumitte xayyosseh sugtek

b) Sumaq warkat akah been madmak iroh geeri taamal asseenik hinnay edde xoqoysimuh geeri xagaral tabseh geytimek

c) Kukti ixximak 985/2009 elle madqen innal aqusbuse week

d) Luulâ taamah eglaalih kukta, madqooqii kee miracsentittek iroh taamitem geytimtek

e) Luulâ taamah egla mano aalle waytam wagiita doolat xagar diggoysek.

2. Ummaan luula taamah egla ta maasayyak 42 nali maasayyak (1)(a-e) roorisen abtootak inkitto hinnay wohuk biso abteh sugtek, wagiita doolat xagar diggoysek sumaq warkat teetik gacsaanah.

6) እገዳ የተደረገበት የኅብረት ሥራ ማህበር የታገደበትን ምክንያት የሚገልፅ ደብዳቤ ከደረሰበት ዕለት አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የታዩ ጉድለቶችን በማስተካከል ማሳወቅ አለበት፣

## 42. የምዝገባ የምስክር ወረቀት ከመዝገብ ስለመሰረዝ

1) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የምዝገባ ምስክር ወረቀት በምከተሉት ምክንያቶች ከመዝገብ ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሃሰት ማስረጃ በማቅረብ መሆኑ ሲታወቅ፣

ለ) የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን ከተሰጠው ዓላማ ውጪ ለሌላ ተግባር ሲገለገልበት ወይም እንዲገለገሉበት ለሌላ አካል አስተላልፎ ከተገኘ፣

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 እና በዚህ አንቀጽአንቀጽ 37 በተደነገገው መሰረት ካልታደሰ፣

መ) ከኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች ውጪ ሲሰራ ከተገኘ፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ህልውናውን ያጣ መሆኑን አግባብ ባለው ባልስልጣን ሲረጋገጥ፣

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አንቀጽአንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 1 ከ ሀ - መ ከተዘረዘሩት ድርጊቶች መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ድርጊቶችን መፈጸሙ አግባብ ባለው ባለስልጣን ሲረጋገጥ የምዝገባ

3. Ummaan luulâ taamah egla wagiitah yan doolat xagar aggiliyyi madqa dacrisak, sumaq warkat duuga waqdi warkat gacissam faxximta.
4. Ta maasayyak 42 nali maasayyak (3) madqeenim anuk sumaq warkat akak duugan eglah naharal elle kutbeh tet yaysixxigeenim faxximta.
5. Ummaan luulah egla wagiita doolat xagar sumaq warkat teetik duugek, sumaq warkat woo ayrot edde gacissam faxximta.
6. Sumaq warkat gacissa egla amoginaa kee ugugubbâ muhri edde gacissam faxximta.
7. Sumaq warkat gacisse luulah egla tet migaaqal fakkimte banki sandug aliftam faxximta. Sandug alfimemih alhum xayyossam faxximta.

## 43) Ayyunti raymih xoqoysimah luulâ taamah eglaali aysaqarriyya

1 Luulâ taamah eglaalih kuktak 985/2009 maasayyak 10 luulâ taamah eglaalih maysaqarrah madqeenim elle anuk ayyunti raymittel xissimta eglaalih ossotinah ayyunti raymittel daddos kee xoqoysih kukti ixximak 1223/2012 maasayyak 10 ugutak ken yaysaqarreenim faxximta.

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን የመፍረስ ሕጉን ተከትሎ ከመዝገብ ሲሰረዝ የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን መመለስ ይኖርበታል::

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ለሚሰረዝበት የኅብረት ሥራ ማህበር እንዲያውቀው አስቀድሞ በጽሁፍ መገለጽ ይኖርበታል::

5) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አግባብ ባለው ባለስልጣን ከምዝገባ ሲሰረዝ የምዝገባ ምስክር ወረቀቱን በዕለቱ መመለስ አለበት::

6) የምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲገለገልባቸው የቆየውን የራስጌና የግርጌ ማህተም አያይዞ መመለስ አለበት::

7) የምስክር ወረቀቱን የሚመልስ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ሲገለገልባቸው የቆየውን በስሙ የተከፈተውን ማንኛውም የባንክ ሂሳብ ቁጥር ማዘጋት አለበት:: ስለመዘጋቱም ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል::

## 43. ስለማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 10 ስለ ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ለሚደራጁት በተጨማሪ በማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደር እና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 1223/2012 አንቀጽ 10 መሰረት በማድረግ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል::

2 Ta maasayyak 139 nali maasayyak 18 ayyunti raymitteh xoqoysimah eglaalih maysaqarra wagsiisak madqeenim elle anuk sinni dirki kibbi heenih aysaqorrah xayyoyta ayyunti raymih xoqoysimah eglaali:

a) Baxsa le maysaqarral yaysaqarrimen
b) Baxsa le maysaqarrâ sumaq keenih yaceen.
c) Magdooda inkih kibe weenik kuktak 985/2009 ugutak elle sugah sumaq warkat keenih aceelon.

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 139 ንዑስ አንቀጽ 18 ላይ ስለ ማህበረሰብ ተፋሰሶች ተጠቃሚዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት ምዝገባ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እሚሏለተው ለምዝገባ የሚመጡ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በኅብረት ሥራ ማህበራት፤

ሀ) በተለየ መዝገብ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
ለ) የተለየ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) መስጠት ይኖርበታል፡፡
ሐ) ሁሉንም መስፈርት ያላሟሉ ሆነው ሲገኙ በአዋጅ 985/2009 መሠረት ጊዜያዊ የምዝገባ ምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

## Lecey heele exxa

## Luulâ taamah eglah adoytiini magdooda, gar kee dirki

## ክፍል ስድስት

## የኅብረት ሥራ ማህበር አባልነት መስፈርቶች፣ መብትና ግዴታ

### 44. Adoyta xiqsissa magdooda

1 Luulâ taamah eglaalih ixximak 985/2009 maasayyak 24 madqimtem elle anuk eglah adoytiinih magdo ciggiltam addat aallele.

a) Madqal gar akak duugumewee hinnay masinkica taqabi aalle waa
b) Luulâ taamah eglah taamah rakaakayal sigoh yan hinnay taamah yani
C) Eglak edde xinta, adda xinto, baxaabaxsa le miracsentitte kee amolladi modod faaticise edde cabooba yagdaboh labbat le

### 44. ለአባልነት የሚያበቁ መስፈርቶች

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 24 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባልነት መስፈርት በተጨማሪነት የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ) በሕግ መብቱ ያልተገፈፈ እና የአዕምሮ መታወክ የሌለበት፤
ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ ክልል የሚኖር ወይም የሚሰራ፤
ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ፣ ውስጥ ደንብ፣ ልዩ ልዩ የአፈጻጸም መመሪያዎችን እና የጠቅላላ ጉባኤ የፀደቁ ውሳኔዎች ለመፈፀም ፍቃደኛ የሆነ፤

c) Tonna celta luulâ taamah eglat gace wee

d) Luulâ taamah egla abta taamoomit booda xoqoysi luk suge waama

2 Ta maasayyak 1 madqimtem anuk, tohuk afal federeshinit adoytah tan yuniyonih adoyta akke wayte rakiibo luulâ taamah egla, luulâ taamah eglaalih federeshinih adoyta yakku xiqtah.

3 Ta maasayyak nali maasayyak (2) madqimtem elle anuk, ta abtoh wagiita doolat xagar fan qokolta alhumitte xayyoysam faxximta.

## 45) Luulâ taamah eglaalih adoytiitih gara

1 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 25(1) madqimtem elle anuk inki adoyti ciggilta garwa le.

a) Amolladi mododut angaluk issi esseedo dimokraasil warsitam, yaybulleem xiqa

b) Adoytit sinni luulah eglak faxinnaan oyti geyaanam duudan

c) Luulah egla wagittaamak, wayto yeelleenik xayyoysaanam, diqan ceela raddi geyaanamih gar lon.

መ) በተመሳሳይ ሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ያልሆነ፣

ሠ) ቀድሞ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ከሚያከናውነው ዓላማና ተግባር ጋር የጥቅም ግጭት በሚኖረው ተግባር ላይ ያልተሰማራ፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አስቀድሞ ለፌዴሬሽኑ አባል የሆነ ዩኑዬን አባል ያልሆነ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር የኅብረት ሥራ ማህበራት የፌዴሬሽን አባል መሆን ይችላል፣

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚሁ ተግባር አግባብ ካለው ባለሥልጣን ደጋፊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል።

## 45. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት መብት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 25 (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የሚከተሉትን መብቶች ይኖሩታል፡፡

ሀ) በጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ላይ በመሳተፍ አቋምን ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልኩ በፊቃደኛነት ማራመድ፣

ለ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው አስፈላጊውን መረጃ የማግኘት

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ማንኛውም ጥያቄ፣ ቅሬታና አስተያየት የማቅረብና መልስ የማግኘት፣

d) Egla tacee aydakaakanitte baxsa sinnim yangaleenimih gar lon.

e) Adoytiinok yewqek meklê suge saamih melleb kaah gacsaanamih gar lon.

f) Faxximta saaqat awlaytu reedisam

2 Ta maasayyak nali maasayyak(1) tanim elle anuk faxe adoyti issi amoh hinnay awlayti madqa kaah kuuxxe garitte geele.

## 46. Luulâ taamah eglaalik adoytit dirki

1 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 25(2) madqimtem elle anuk kulli adoyti ciggilta dirkiika le.

a) Amolladi mododih edde caboobal waktil geytimak celta gabat agle abaama.

b) Eglah tayseeh, maxxat meqe murti hinnay ayfaf waktil xayyoysaama

c) Adoytit luulah eglak been mago wakti tatre kal yaceenimi

d) Amolladi mododul adoytit faaticisseh tan cogaysoosa waktil gaba kaltuh qoklaanam kee kattaataanam keenil tan

e) Adoytiitih tan tamlisen taameynit kulli adoytih innah keenih yeceen taama kee qaaqak yawqeenimi.

f) Luulah egla kasaarittek woo kasaara kurrasitaanama.

g) Eglak addâ saay diggoysaanama

መ) አባላት ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው ስልጠናዎች ላይ ያለ ልዩነት የመሳተፍ፣

ሠ) አባልነት ሲቋረጥ የተከፈለውን የዕጣ ዋጋ መልሶ የመካፈል፤

ረ) አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ተወካይ መሾም፣

2) በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል በራሱ ወይም በተወካዮቹ አማካኝነት በህግ የተሰጠውን መብቶቹን ያገኛል፤

## 46. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት ግዴታ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 25 (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል የሚከተሉትን ግዴታዎች ይኖሩታል::

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤው በሚወስናቸው ውሳኔዎች ላይ በወቅቱ በመገኘት ተገቢውን ተሳትፎ ማድረግ፣

ለ) አባላት ለኅብረት ሥራ ማህበራቸው የተሻለ እና ጥራት ያለው ምርት ወይም አገልግሎት በወቅቱ የማቅረብ፣

ሐ) አባላት ከኅብረት ሥራ ማህበራቸው የተበደሩትን ብድር የመከፈያው ጊዜ ከማለፉ በፊት መመለስ፣

መ) በጠቅላላ ጉባኤ አባላት ውሳኔ የታቀዱ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ድጋፍና ክትትል የማድረግ፣

ሠ) አባል የሆኑ ቅጥር ሠራተኞች እንደ ማንኛውም አባል የተሰጣቸውን ተግባርና ኃላፊነት መወጣት፣

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ኪሳራ የመካፈል፣

ሰ) አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ የውስጥ ሰላም እንዲረጋገጥ የማድረግ፣

h) Eglak edde xinti madqa yaxmiqeenim kee yassakaxxeenimi

i) Eglak, migaq yaysaamme, xoqoysit kee boola le abtok yaxxeereenimi.

j) Luulâ taamah eglah miraacinnuh kaxxa qokol abaanama

k) Eglalluk aben ambalal aamantil yassakaxxeenimi

l) Luulâ taamah eglah ikoyta dacrisaanama.

2 Ta maasayyak 1(a-l) fan madqimtem elle anuk issi dirkik awqe weeh yan ummaan adoyti luulâ taamah eglah edde xintal faaticisaanamak ugut abak esserimele.

## 47) Luulâ taamah adoytit, adoytiinuk xiiriyaanam wagittaama

1 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 26(1 kee 3) madqimtem elle anuk adoyti eglak xiiriyimam ciggilta caagiida takke waqdi

a) Adoyti rabe kaa tekkek

b) Luulâ taamah egla tiddigillek

c) Adbi sinna baahek

d) Adoytak faxximta(esseran) abud mekeluh labbat aalle week

e) Sittallakleh 3 daffeynal sabab maleh geytime week

f) Luulah eglah madmal saduh yan abinat assekaa tekkek

ሸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ መረዳትና ማክበር፤

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ጥቅም፣ ገጽታ፣ አሠራር ወይም አፈጻጸም ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር የሚችል ማንኛውንም ድርጊት ወይም ግድፈት የማስወገድ፤

በ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር ከፍተኛ ትብብር ማድረግ፣

ተ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር የሚያደርገውን ማንኛውንም የውል ቢታማኝነት የማክበር

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ንብረቶች የመጠበቅ፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ቸ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ግዴታውን የማይወጣ ማንኛውም አባል የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ በሚወሰነው መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፤

## 47. የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ከአባልነት ስለመሰናበት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 26 ከንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባል ከኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚሰናበተው በተጨማሪነት በሚከተሉት ጉዳዮች ይሆናል፤

ሀ) አባል ግለሰብ ሲሞት

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲፈርስ፣

ሐ) የዲሲፕሊን ጉድለት፣

መ) አባል የሚፈለግበትን የብድር ዕዳ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ፣

ሠ) ለሦስት ተከታታይ መደበኛ ስብሰባ ያለ በቂ ምክንያት ያልተሳተፈ፣

ረ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ዓላማና ተግባር ጋር የሚፃረር ተግባር የፈፀመ፤

g) Luulâ taamah eglak xaaman uwwitte hinnay yaylammen uwwitte isi xoqoysih taagah addah yeylemmek, fulah yeylemmek hinnay isih abewaamah absiisek tonnaal maxxat yoysoomek

2 Ta maasayyak 47 nali maasayyak (1)(d) madqimtem elle anuk abud mekeluh fayxi aalle week rakaakay tekkek kaxxa caxal hinnay federal tekkek qimbo caddoh cokmi caxal kaak malkitak akah gacsa innah aban

## 48) Qusba adoytit takku awwalih adoytit qagitak adoytiinuh yakkuqeenim wagittaama

1 Dumih adoyti eglak adoytah yaduurem faxek bicsen cibta kibak assabalta taama miraacissa maroh xayyoysu duudah.

2 Adoyti abe esserok ugutak kaa yakkuqenik afal ciggilta caagiida kusaaqise lon.

a) Adoytiini essero baahe num eglak taama rakaakayal yanik waytam
b) Geeri luulah eglak abud kaat ane waamih alhum xayyoysek
c) Duma edde suge luulah eglah akah xiiriyimem tamixxigem faxximta (bicsen cibtal roorisak yaktube)
d) Qagitak luulah eglat akah yaduure sabab bicsen cibtal kiba

ተ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚያቀርበውን ምርት ወይም የአገልግሎት ዋጋ በማይገባው ሁኔታ ለማግኘት ጥራቱን ያጓደለ ወይም መጠኑን የቀነሰ፣

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 47 ንዑስ አንቀፅ 1 (መ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕዳውን ለመክፍል ፈቃደኛ ካልሆነ በክልል ከሆነ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም በፌዴራል ከሆነ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠይቆ ዕዳውን እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

## 48. አዲስ አባላትን እና የቀድሞ አባላትን እንደገና ስለመቀበል

1) የቀድሞ አባላት ዳግም ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ለመመለስ በተዘጋጀው የአባልነት ማመልከቻ ቅፅ መሠረት ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት ጥያቄውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) አባሉ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት አባል ከመሆኑ በፊት የሚከተሉት ጉዳዮች የሚጣሩ ይሆናል፤

ሀ) የአባልነት ጥያቄ አቀራቢው በኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ክልል ውስጥ ስለመገኘቱ፣
ለ) በሌላ ኅብረት ሥራ ማህበር የብድር ዕዳ የሌለበት ስለመሆኑ መረጃ ሲያቀርብ፣
ሐ) ቀደም ሲል ከኅብረት ስራ ማህበሩ የተሰናበተበት ምክንያት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት ዝርዝር መረጃ በማመሳከር መሙላት፣
መ) ዳግም ወደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚመለስበት ምክንያት በተዘጋጀው ፎርም መሠረት መሙላት፣

3. Luulâ taamah eglah taama miraacissa maro adoytiini essero yakkuqeenih cinaanam argaquk edde cabo tatrusanam duudan

4. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 26 nali maasayyak (4-7) fan madqimtem elle anuk awwalih adoytit yadaaronuh taama miraacissa maro keenih oggoltek edde xinti madqah addal elle tan innal maysaqarrâ meklaa kee saami mellebik ramma itta mekla meklaanam faxximta.

5. Ta maasayyak 48 nali maasayyak 4 madqeenim elle anuk qusba mari hinnay qagta mari maysaqarrah meklaanam dumaak amolladi mododul faaticiseenimi dubuk.

6. Luulâ taamah eglat qusubih adoytiinuh yukkuqen adoyti maysaqarra kaak aben ayrook xabba haanam gar kee dirki kaah dacarsimak ummaan adoyti eglak geyah yan xoqoysii kee affaafay geyam duudah.

## 49) Rakiibo luulâ taamah eglaalih adoytiitik ugutmah ixxu elle yargiqen inna

1 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 7 nali maasayyak (2 kee 3) kee maasayyak 8 nali maasayyak (1) madqenim elle anuk murti taamal hinnay ayfaf taamal hinnay nammam inkih abta luulâ taamah eglaalih adoytit ugtuma ixxi keenik elle ciggiltannal anele.

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የአባልነት ጥያቄ ላቀረበው አካል አባል የመሆን ወይም ያለመሆን ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡

4) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 26 ከንዑስ አንቀፅ 4 እስከ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ አባላት ዳግም እንዲመለሱ በሥራ አመራር ኮሚቴ ሲፈቀድላቸው በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ የተወሰነውን መመዝገቢያ እና ዝቅተኛውን የዕጣ ዋጋ ከፍያን መፈጸም አለበት፡፡

5) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 48 ንዑስ አንቀፅ 4 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ ወይም ዳግም የተመለሱ የቀድሞ አባላት የሚከፍሉት የመመዝገቢያ ክፍያ ቀድሞ በጠቅላላ ጉባዔ የተወሰነው ብቻ ይሆናል፡፡

6) በኅብረት ሥራ ማህበሩ በአዲስ አባልነት ተቀባይነት ካገኘበትና ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ መብትና ግዴታዎቹ ተጠብቀው እንደ ማንኛውም አባል ኅብረት ሥራ ማህበሩ በሚሰጣቸው አገልግሎት መጠቀም ይችላል፤

## 49. የመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት መነሻ ቁጥር አወሳሰን

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 እና 3 እና በአንቀፅ 8 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት ወይም በማምርት እና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የተሰማሩ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር እንደሚከተሉትን ይሆናል፤

a) Saq kee laciimil xissimta luulâ taamah eglaalih adoytiitik ugutma 80 sahdaytu

b) Buqree kee garbok orobtaamal xissiima marak ugutma 100 sahdaytu akkele.

c) Dariifal rekitak xissimta xaamitah eglah ugut 250 sahdaytu akkele.

d) Maakaadol rekitak xissimte xaamitah egla tekkek 100 numuk xissimta

e) Rakaakayal rekitak xissimta maali qedaddo kee abud eglaalih adoytit ugutma 100 numu.

f) Makaadol rekitak xissimta maali qedaddoo kee abud eglaalih adoytit 80 numu

g) Sigo qarwah luulâ taamah eglah xissiima adoytit ixxima magaalal 50 num barril 24 num akkele.

h) Mangaafa buqre abah eglak ugutma 250 numu.

i) Caxaaxuwaa kee caxfeexu yabqure marih ugutma 50 numu

j) Sissin maytani gaddaa kee yambaxe gaddal xissiima marih ugtuma wagiita doolat xagar argiqele. Takkay immay ugutmah ixxi 10 numuk adda hinna.

ሀ) በእንስሳት እና እንስሳት ተዋፅኦ የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር 80 ሰው ይሆናል፡፡

ለ) በሰብል እና የደን ውጤቶች የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት የመነሻ ቁጥር 100 ሰው ይሆናል፡፡

ሐ) በአከባቢ መሰረት አድረገው የሚደራጁ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 250 ሰው ይሆናል፡፡

መ) ተቋምን መሰረት አድረገው የሚደራጁ የሸማቾች የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 100 ይሆናል፡፡

ሠ) በአከባቢ መሰረት አድረገው የሚደራጁ በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 100 ሰው ይሆናል፡፡

ረ) ተቋምን መሰረት አድረገው የሚደራጁ በገንዘብ ቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የአባላት የመነሻ ቁጥር 80 ሰው ይሆናል፡፡

ሰ) በመኖሪያ ቤቶች የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር በገጠር 50 በከተማ 24 ይሆናል፡፡

ሸ) የሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር 250 ይሆናል፡፡

ቀ) በአትክልትና ፍራፍሬ እና በመስኖ ሥራዎች ላይ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚደራጁ አባላት የመነሻ ቁጥር 50 ይሆናል፡፡

በ) የተለያዩ ቀሚ እና አላቂ ሀብቶችን መሰረት አድርገው የሚደራጁ የኅብረት ሥራ ማህበራት ባለው ሀብት እና በአዋጭነት ጥናት መሰረት የመነሻ ቁጥሩን አግባብ ያለው ባለስልጣን ይሰናል፡፡ ሆኖም መነሻ ቁጥሩ ከ10 ሰው ማነስ አይችልም፡፡

## 50) Adoytit maysaqarrah bicsa wagittaama

1 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 28 madqimtem elle anuk adoytit maysaqarra ossotinah ciggiltam addat le.

a) Rihim caagid
b) Buxa marih manga
c) Raatibik le taama
d) Xaame saamih qaynatah hinnay lakqoh
e) Rakiibo luulâ taamah eglak daga tekkek, adoytah edde tan luulah eglah migaq, adoytit manga, nado, daalooli manga kappitala, qedaddo, edde xissiime edde tiddigile liggida kee ayro, adoytit maysaqarrah cibta xakabah tan.

2 Edde xintal tan geeri ximmooma.

## 50. የአባላት መዝገብ ስለ ማደራጀት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 28 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የአባላት መዝገብ በተጨማሪነት የሚከተሉትን ይይዛል፤

ሀ) የጋብቻ ሁኔታ፣ 44
ለ) የቤተሰብ ብዛት፣
ሐ) መደበኛ ስራ፤
መ) የገዛው ዕጣ በዓይነት ወይም በገንዘብ፤
ሠ) ከመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር በላይ ከሆነ የአባል ኅብረት ሥራ ማህበር፤ ስም፣ የግለሰብ አባላት ብዛት፣ ፆታ የቤተሰብ ብዛት፣ ካፒታል፣ ቁጠባ፣ ተቋቋመበት እና የፈረሰበት ቀንና ዓመተ ምህረት፡፡ የአባላት መዝገብ ፎርም በመመሪያው የአዝል ክፍል ውስጥ ተያይዟል፡፡

2) በመተዳደሪያ ደንቡ የተወሰኑ ሌሎች ዝርዝሮች፡፡

## 51) Luulâ taamah eglaalih adoytit awlaytul xongolo elle yaceen inna

1 Kukti ixximak 985/2009 maasayyak 29 nali maasayyak (3-6) fan madqeenim elle anuk rakiibo luulâ taamah egla, eglaali yuniyon kee eglaali federeshin amolladi mododih adoytit awlisak xongolo yaceenim duudan.

## 51. ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት በውክልና ድምጽ አሰጣጥ

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 3-6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር፣ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን እና የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን የጠቅላላ ጉባኤ አባላት በውክልና ድምፅ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2 Ta maasayyak 51(1) madqimtem elle anuk adoytit sinni labbataak, keenil lon kibalaak ugutak, awlak, yaaxigen tu xiiqik ugutak, ken gabat aglek ugutak amolladi mododul geytima awlaytit dooraanam xiqaanah.

3 Luulâ taamah eglaalih kukti ixximak 985/2009 maasayyak 29(3) madqimtem elle anuk rakiibo luulâ taamah eglah adoytit mangak 500 amo yekkeenik amolladi modod awlaytiinul yakkem duudah. Takkay immay rakiibo luulâ taamah eglak inki num awlisam duudam bisoh intek 500 numu.

4 Ta maasayyak 51(3) amolladi mododih awlisentat yabta madqa elle anuk, awliinul takke rakiibo luulâ taamah egla amolladi mododih adoytit mangak 100 daga yakkeenim maduudan.

5 Amolladi mododuh takke awlisso luulâ taamah egla leh tan adoytit mangal qekitak yargiqeenimi. Qaduk yambulle gital cubbussol takkem faxximta.

6. Ummaan luulâ taamah eglak adoyti ixxi dagal edde yaabeenimik biso yekkek teknolojit xoqoysimak amolladi modod gexsaanam duudaanah.

7. Luulâ taamah eglah caalatak ugutak baar le awliinoh gexso wagsiisak amolladi modod argaquk edde xin madqal haysitak abinal assaanam faxximta.

2) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አባላቱ በራሳቸው ሙሉ ፍላጎትና እምነት መሰረት የተወካዮችን ታማኝነት፣ ውሳኔ ሰጭነት፣ ባላቸው የንቃ ተሳትፎ፣ በምሳሌነታቸው እና በሌሎች ተዛማጅ መስፈርቶች በመነሳት በጠቅላላ ጉባዔ ላይ የሚሳተፉ አባላትን ሊወክሉ ይችላሉ፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀጽ 29 ንዑስ አንቀፅ 3 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ቁጥር ከ500 በላይ ከሆነ የጠቅላላ ጉባኤ በውክልና ሊካሄድ ይችላል፡፡ ሆኖም በመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አንድ ተወካይ የሚወክላቸው አባላት ቁጥር ከፍተኛው ከ500 ሰው በላይ ሊሆን አይችልም፣

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ስለ ጠቅላላ ጉበኤ ውክልና የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውክልናን መሰረት አድርጎ የሚካሄድ የማንኛውም የመሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ብዛት ከፍተኛው 1000 አባላት ሊበልጥ አይችልም፣

5) የሚደረገው የጠቅላላ ጉባኤ ውክልና አሰጣጥ እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ አባላት መጠን የሚወሰን ሆኖ ግልፅነት ያለው አሳማኝና በጥናት ላይ የተመሰረት መሆን አለበት፣

6) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የአባላት ቁጥር ከተጠቀሰው በላይ የሚሆን ከሆነ ለዚህ ተግባር ሊሆን የሚችል ቴክኖሎጅ በመዘርጋት እና ቴክኖሎጅውን በመጠቀም የጠቅላላ ጉባዔ ማካሄድ ይቻላል፡፡ ስለ አፈፃፀሙና አጠቃቀሙ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊወስኑ ይችላሉ፣

7) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ዝርዝር የውክልናውን አካሄድ በተመለከተ በጠቅላላ ጉባዔ ተወስኖ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ በማካተት ተግባራዊ መደረግ አለበት፣

8. Ta maasayak 51(6 kee 7) madqimtem elle anuk ummaan luulâ taamah eglaalih yuniyonih amolladi modod elle ukkummootam kulli rakiiboh eglak inki awlaytu luk kinni waqdi kulli luulah taamah egla leh tan adoytit mangak ugutak ossotinah awlaytitte yaalloonu xiqaanah ossotinah ruuban awlaytitte elle awlisan miracsenta xakabuh tan.

9. Ta maasayyak 51(8) madqeenim elle anuk luulâ taamah eglaalih yuniyonih adoyta yakke geeri luulâ taamah eglah yuniyon yaalluwaah yan amolladi mododih awlaytiino taban kee numuk tatram maduuda.

10. Ta maasayyak 51(6 kee 7) madqimtem elle anuk luulâ taamah eglaalih federeshinik amolladi modod elle xissiimam kulli yuniyonuk yamate inki inki adoytiiti awlaytiino. Inki inki yuniyon adoytiitik mangom yeellek ossotinah awlaytit ruubaanam xiqqimtah. Ossotinah awlaytit elle ruuban gurri (miracsentak ugutak) takayruh yan.

11. Baxsa le rakiibo luulâ taamah eglaaliy federeshinit saanih tangele tan. Woo eglaali namma namma awlaytu awlisan.

8) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን ጠቅላላ ጉባኤ የሚመሰረተው ከእያንዳንዱ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር አንድ ተወካይ የሚኖረው ሲሆን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ የአባላት ብዛት ተጨማሪ ተወካይ የሚኖረው ይሆናል:: የተጨማሪ ተወካዮችም አወካከል ዝርዝር በመመሪያው እዝል ውስጥ ተያይዟል::

9) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 8 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አባል የሚሆን ሌላ የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የሚኖረው የጠቅላላ ጉባኤ ውክልና ከአስራ አንድ ሊበልጥ አይችልም፣

10) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 51 ንዑስ አንቀፅ 6 እና 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን የጠቅላላ ጉባኤ የሚመሰረተው ከእያንዳንዱ አባል የኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን አንድ ተወካይ የሚኖረው ሲሆን እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬን የአባላት ብዛት ተጨማሪ ተወካይ የሚኖረው ይሆናል:: የተጨማሪ ተወካዮችም አወካከሉ በመመሪያው እዝል ውስጥ ተያይዟል::

11) በልዩ ባህሪያቸው በቀጥታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ፌዴሬሽን አባል የሚሆኑ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት እያንዳንዳቸው ሁለት ተወካይ ይኖራቸዋል::

12. Ummaan luulâ taamah eglah edde cabo elle taturtam xongolo kinnuk mododuk mango gaba geytimtam faxximta. Mododuk mango gabah xongoloh acwa wagittam kulli luulâ taamah eglaali sinni caddol edde xinti madqat culsaanam faxximta.

13. Awlaytit koboxul xongolo yaceen waqdi ken awlisitte adoytiitih gar edde kassitaanam faxximta.

14. Awlaytit qilsi caagiidal xongolo yaceen waqdi luulâ taamah eglaalik taama miraacissa maro, adoytit inkih edde tangaluh sigoh 'aroocal, taamah aroocal xongolo kobxisoonuh teknolojit xoqoysimak xongoloh acwa koobaahissam duddah.

15. Amolladi mododih kobox luulah eglah awlaytit gitaak xongolo yaceenim takke way xongoloh acwa dimokraasi radmol gexsittam yasmiteenim faxximta.

16. Ummaan luulâ taamah eglah addal taturta edde cabooba xongolo mangal taturta. Takkay immay xongolo missa tekkek miraacise yacee xongolo aysuk raqta.

17. Luulâ taamah eglaaliilluk taamitta adoytit maritte xongolo taceemih gar malon.

18. Amolladi mododih awlayti amolladi mododih edde cabok ugutak faxe waqdi awlaytiinok kalla kaa heenih geeri num edde haanam duudan.

12) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ውሳኔ የሚተላለፈው በአባላት በአብላጫ ድምፅ ሆኖ የምልዓተ- ጉባዔ ወይም ኮረም መሟላት ይኖርበታል:: የምልዓተ- ጉባዔ ወይም ኮረም መሰረት ያደረገ የድምጽ አሰጣጥ ሂደትን በተመለከተ እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት አይነት እና ደረጃ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ ሊወሰኑ ይገባል::

13) ተወካዮች በስብሰባዎች ጊዜ የሚሰጡት የውሳኔ ድምፅ የወከላቸውን ሰዎች መብት ከግምት በማስገባት ሊሆን ይገባዋል::

14) ተወካዮች ወሳኝ በሆኖ ጉዳዮች ላይ ድምፅ በሚሰጥበት ሂደት የኅብረት ሥራ ማህበራት ስራ አመራር ኮሚቴ ለአባላት ተደራሽ በሚሆን ሁኔታ በመኖሪያቸው ወይም በስራቸው ቦታ ከተወካዮቻቸው ጋር በመቀናጀት ድምፅ የሚሰባሰብበት ወይም ሌሎች በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ የድምፅ አሰጣጥ ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ ይችላል::

15) የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ በኅብረት ሥራ ማህበራት ተወካዮች አማካኝነት በውክልና ድምፅ የሚሰጥ ቢሆንም የድምፅ አሰጣጡ የዲሞክራሲያዊ መርሆዎች በጠበቀ ሁኔታ መከናወኑን ኅብረት ሥራ ማህበራት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል::

16) በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይሆናል:: ሆኖም የድምፅ አሰጣጡ እኩል በእኩል ከሆነ የጉባዔ ሰብሳቢ የሚሰጠው ድምፅ ወሳኝነት ድምፅ ይሆናል::

17) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ጋር በተለያዩ ሁኔታዎች ተጣምረው የሚሰሩ አባል ያልሆኑ ግለሰቦች ድምፅ የመስጠት መብት የላቸውም::

18) የጠቅላላ ጉባዔ ተወካይ በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ መሠረት በማንኛውም ወቅት ወከልናው ተነስቶ በሌላ ሊተካ ይችላል::

19. Luulâ taamah eglah edde xintal baxsa luk daffeyteh akke waytek raatib hinnay amok rada mododul tatrusan edde cabooba, daffeynal geytimtam faxxiima adoytiitik mango gabah rubtal tatrusan.

20 Awlaytit dooroo kee awlaytit abtoo kee qaaqa wagittam eglak edde xin madqal faaticisan.

## Malcin heele exxa
## Luulâ taamah eglak amolladi mododu, taama miraacissa maro, taama gexse kee tamlisen mihrat leela wagittaama.

### 52) Amolladi mododih esseedo

1 Ummaan luulâ taamah eglak amolladi mododih ciggilta esseedo aallele.

a) Amolladi mododu iyyaanam kulli adoyti hinnay awlayti amoh elle geytima daffeyna (koboxu)

b) Luulâ taamah eglah caagidil amolladi modod tatrusa edde cabo maggaraqqa kinni.

c) Ummaan luulâ taamah egla raatib modod taallem faxximta. Tonnaah amok radah takke modod kee baxsa le amolladi modod taallem bicta.

d) Amolladi modod irgiqqi haytaamih reeday nabah iyyak garab taama

19) በኅብረት ሥራ ማህበራት መተዳደሪያ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተገለጸ በስተቀር በመደበኛ ወይም በአስቸኳይ ጉባዔ የሚተላለፉ ውሳኔዎች በስብሰባው መገኘት ካለባቸው አባላት አብላጫ ድምፅ የሚወሰን ይሆናል፡፡

20) የተወካይ አባላት አመራረጥን እና የተወካይ አባላት ተግባርና ሃላፊነት በተመለከተ በኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ የሚወሰን ይሆናል፣

## ክፍል ሰባት
## ስለኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባዔ፣ የሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ስራ አስኪያጅ እና ተቀጣሪ ባለሙያዎች

### 52. የጠቅላላ ጉባኤ አቋም

1) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ የሚከተሉት አቋም ይኖሩታል፤

ሀ) ጠቅላላ ጉባኤ ማለት እያንዳንዱ አባል ወይም ተወካይ በማንባር ወይም በአካል የሚገኝበት ስብሰባ ነው፣

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጉዳይ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ የሚያስተላልፈው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

ሐ) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር መደበኛ ጉባዔ ሊኖረው ይገባል፡፡ ሆኖም እንዳስፈላጊነቱ አስቸኳይ እና ልዩ የጠቅላላ ጉባዔ ሊኖረው ይችላል፡፡

መ) የጠቅላላ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ከፍተኛ ስልጣኑን በከፊል ለስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. Faxe luulâ taamah eglah adoyti kaal tan mekla inkih acuyyu hee week luulâ taamah eglah amolladi mododol hinnay taama miraacissa maroh doorot yangalem maduuda.

3 Ummaan luulâ taamah egla liggidi amolladi modod abtak afat yan taban kee koona ayroh addat qusba adoytit culussam mafaxximta.

## 53 . Amolladi mododih reeda kee abto

1 Luulâ taamah kukti ixximak 985/2009 maasayyak 32 madqimtem elle anuk luulâ taamah eglak amolladi mododih abtoo kee reeda ciggiltam aallele.

a) Taturte daffeynah guuma ankacissi faaticissi haan.

b) Taama miraacissa maroh edde cabol waaga le adoytiitih caagid wagtan. Amolladi modod margaqa elle yacayuh xayyoysan. Tonna kinnuk ta waaga mododuk afat namma ayrok afat taama miraacissa maroh kutbe abeynih katuuk kutbeh xayyowtam faxximta.

c) Luulâ taamah eglak qaklissa malah buxa lowsis maro, taama miraacissa maro dooranam, tonnaah issi reedat xoqoysimak reedak kalaanam targiqe.

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሆኖ የሚጠበቅበትን ክፍያ ካላጠናቀቀ በቀር በኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ ወይም በሥራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ ላይ መሳተፍአይችልም።

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤው ከመደረጉ በፊት ባሉት አስራ አምስት ቀናት ውስጥ አዳዲስ አባላትን ማስገባት የለበትም።

## 53. የጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 32 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ጠቅላላ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉትን በተጨማሪነት ይይዛል፤

ሀ) ያለፉውን ጊዜ የጠቅላላ ጉባኤ ቃለ ጉባዔ በማድመጥ ሪፖርቱን ያፀድቃል፡፡

ለ) በስራ አመራር ኮሚቴ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያላቸው አባላት ጉዳይ በጠቅላላ ጉባዔ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያቀርባል፡፡ ሆኖም ቅሬታው የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ከመደረጉ ቢያንስ ሁለት ቀናት በፊት ለስራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበር የአማካሪ ምክር ቤት፣ የስራ አመራር ኮሚቴ እና ቁጥጥር ኮሚቴዎችን የመምረጥ እንዲሁም ስልጣኑን ተጠቅሞ ከኃላፊነት ማንሳት መወሰን፤

d) Luulâ taamah eglaalih adoytih leh yan investimenti, gaddi buulok lonum kee abud fayxih celta edde cabo tatrussa.

e) Wagiita doolat xagarak iroh tan ooxiterwa mekla amolladi modod faaticisa. Takkay immay oxiterwak qaaqa, taamaa kee mekla wagittam edde xinti madqah addal tanim faxximta.

f) Amolladi mododul ooxit waqdi geytimtem kee edde culse ween cisab ammuntitte wagsiisak ugutta esseroorah ooxiter gacsa aba.

g) Taama miraacissa marok xayyoowe gabbaaquk ugutak eglah adoytit bahteemih elle digalsiman gurraa kee diiriyyo faxximtek kaadu elle cabo margaqa yaceen.

h) Adoytit, tamlisen taameynit barittoo kee aydakaakan akah geyan innah maclan.

i) Luulâ taamah eglah taama gexseh tamlo faaticisan.

j) Baxsa le taamoomih hinnay cogayso yagdaboonuh (tagdube maroh adoytit) yakkoonuh modod addak dooran. Aban taamaa kee sugaanah gide waktik yargiqen.

ሠ) አግባብ ካለው ባለስልጣን ውጭ ባሉ ኦዲተሮች ሂሳባቸውን ሲያስመረምሩ በሚደረጉ ስምምነት ሰነዶች ላይ የኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ በጠቅላላ ጉባዔ የሚፀድቅ ይሆናል፡፡ ሆኖም ስለ ኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ሊወሰን ይገባል፡፡

ረ) ከጠቅላላ ጉባዔው በኦዲት ግኝቱ እና ባልተካተቱ የሂሳብ ርዕሶች ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች ኦዲተሩ ምላሽ ይሰጣል፣

ሰ) ከሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብለት ሪፖርት መሠረት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ውስጥ አባላት በፈጠሩት ጥፋት የሚቀጡበት እና የሚሰናበቱበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፣

ሸ) አባላት፣ ቅጥር ሠራተኞች ትምህርት እና ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ አሲኪያጅ ቅጥር ያፀድቃል፡፡

በ) እንደአስፈላጊነቱ ልዩ ለሆኑ ተግባራት ወይም ፕሮጀክቶች በኮሚቴ አባልነት የሚሰሩ ከጠቅላላ ጉባዔ አባላት በመምረጥ የሚያከናውኑትን ተግባር እና የጊዜ ቆይታ ይወስናል፡፡

ተ) አዳዲስ አባላትን ይቀበላል፣ ችግር ያለባቸውን ወይም በፍላጎታቸው መሰረት አግዶ ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ያሰናብታል፣

k) Qusba adoytit takkuqeh, sinni labbatak caboonu, taqbik yawqe adoytit rubsussa

l) Luulâ taamah eglak liggidi baajet, kabxah ekraaro kee magcagur ekraaro faaticissa

2 Ta maasayyak nali maasayyak 1(a-j) madqimtem elle anuk luulâ taamah eglaalih yuniyon amolladi mododih caddol yargiqen caagiida afal elle rakiiboh eglaalih caddol walalla iyyeenih yirgiqeenih baahanam faxximta.

3 Yuniyonuk amolladi modod tatruse edde cabol waaga le rakiiboh egla tenek xayyoysittam duddah.

4 Amolladi modod hinnay taama miraacissa marok daffeynah ayro arac saaqat kee ajanxa dagnal 15 ayrok afal kutbeh yaysixxigeenim faxximta.

## 54) Taama miraacissa maroh adoytit dooro, magdo kee iyyin gubat yaniinim

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 34(1 kee 6) madqimtem elle anuk eglak edde xin madqa elle itta innal taama miraacissa maroh adoytiitih magdot ossotinah ciggiltam aallele.

ተ) አዳዲስ አባልትን ይቀበላል፣ ችግር ያለባቸውን ወይም በፍላጎታቸው መሰረት አግዶ ከኅበረት ሥራ ማህበሩ ያሰናብታል፣

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓመታዊ በጀት፣ የንግድ ሥራ ዕቅዶች እና ስትራቴጂክ ዕቅዶችን ያፀድቃል፣

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-በ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ጠቅላላ ጉባኤ ደረጃ በሚወሰኑ ጉዳዮች አስቀድሞ አባል መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት በጉዳዮቹ ላይ በመወያየት ጽድቆ እንዲመጣ ማድረግ ይኖርበታል፣

3) በኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን የጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር መሰረት በተላለፉ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም መሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ቅረታውን ማቅረብ ይችላል፣

4) የጠቅላላ ጉባኤ ወይም የሥራ አመራር ኮሚቴ የስብሰባ ቀን፣ ቦታ፣ ሰዓት እና አጀንዳ የሚገልጽ ግልጽ አጭር ማስታወቂያ ቢያንስ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት ማሳወቅና መጥራት አለበት፣

## 54. የስራ አመራር ኮሚቴ አባል የምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወስኑት የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት ላይ በተጨማሪነት የሚከተሉት ሊያካትት ይችላል፤

a) Taama miraacissa maroh adoyti luulâ taamah eglah adoyta yekkek

b) Madqal tanih tan adoytiini dirkiik kibba hee numu

c) Kaah yeceen qaaqak duddaluk yawqe numu

d) Sinam qoklaanam kicnaah, goori le numu

e) Ahak duma qamal umaanel, hinnay aamanti sinnah malkit akak ane waa numu

f) Atlaakê sababah malkitil anewaa num yakkeemi

g) Rakiiboh eglak miraacissa maroh adoytiinuh $8^{to}$ lem faxximta yuniyonuh tekkek $10^{to}$ yaallem faxximta

h) Barte marih cayli elle dago aroocal dagnal yakriyeh yaktubem faxximta yuniyonuh $8^{to}$ lem faxximta.

i) Keenih yaceen barittoo kee aydakaakay beyuh labbat lem faxximta.

j) Meqem kabanal adoytit akah sumaaqittaah, aamanti lem faxximta.

k) Miraacissa marot anuk margaqa yaceen waqdi tanih tan qaaqaa (esserim) nagay yixmiqe num yakkeemi.

l) Taama miraacissa marot doorimuh dagnal inki liggida luulah adoyta yakkem faxximta.

m) Kaah yaceen amri akkaquk yagdabuh gidmi lem faxximta

ሀ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆነ፣

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች በብቃት የሚወጣ፣

ሐ) የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ በመስራት መወጣት የሚችል፣

መ) ሰዎችን ለመርዳት ፅኑ ፍላጎትና ተቆርቋሪነት ያለው፣

ሠ) ቀደም ሲል በምግባረ ብልሽነት ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የሌለበት፣

ረ) በስነ-ምግባር ወይም በእምነት ማጉደል በክስ ላይ ያልሆነ፣

ሰ) የትምህርት ደረጃ ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢያንስ 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ ሲሆን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩን ቢያንስ10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ፣

ሸ) የተማረ የሰው ሃይል በማይገኝበት ቦታ ለመሰረታዊ ኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ ማንበብና መፃፍ የሚችል ለኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዩኖች 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀ፤

ቀ) የሚሰጣቸውን ትምህርትና ስልጠና ለመውሰድ ፈቃደኛ የሆነ፣

በ) በመልካም ስነ ምግባሩ እና በታማኝነቱ በአባላት የተመሰከረለት፣ 48

ተ) የስራ አመራር ኮሚቴ አባል ውሳኔ በመስጠት ሂደት ያለባቸውን ተጠያቂነት በአግባቡ የተሩዱ፣

ቸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አመራር ሆኖ ለመመረጥ ቢያስን ለአንድ የሥራ ዘመን በአባልነት መቆየት ይኖርበታል፣

ነ) የሚሰጠውን ተግባር ተቀብሎ ለመተግበር ቁርጠኛ የሆነ፣

2. Adoytit kinnaane sabbatah, maddur qaku loonumuh, siyaasa mablah sabbatah, doorime ken kalaanam maxiqta.
3. Taama miraacissa maroh adoytit dooroonuh, 3 adoyta le dorsis maro amolladi modod doora.
4. Luulâ taamah egla miraacisak suge naharsi mari sinni reeda dorsis marol tabsan. Takkay immay wagta doolat xagar doorol shakki yeellek dorsis maro isih dorsiisam duudah.
5. Namma adda doorimak sinni uddur selle mirocti qagitak madooriman. Takkay immay inki uddur tatreek lakal doorimaanam duudaanah.
6. Doorô siirat yamaquh wagiita doolat xagar kattatah qoklah.
7. Marot gacta gid akak iyyan adoytit mangak fulussu heenih mango mara qalalisaanam duudaanah addak meexoonuh.
8. Taama miraacissa maroh manga eglak edde xintal yargiqeenim kinnuk ta maroh adoytiitih manga guba raqta nali maroorah ixxu taallem faxximta. Macaay saqalak kalih adoytit nali maroorah saqolti yakkeenimih taagah.

2) አባላት በማንነታቸው፣ በኢኮኖሚ አቅማቸው እና የፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ከመመረጥ አይከለከሉም፣

3) የስራ አመራር ኮሚቴ ምርጫ የሚያከናውኑ ሦስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል::

4) ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሲመሩ የነበሩ ነባር አመራር አካላት የምርጫውን ስነስርዓት እንደያከናውኑ ስልጣናቸውን ለአስመራጭ ኮሚቴ ያስረክባሉ:: ሆኖም አግባብ ያለው ባለስልጣን በምርጫው ሂደት ላይ ጥርጣሬ ካለው አስመራጭ ኮሚቴውን ሊያስመርጥ ይችላል::

5) ለሁለተኛ ጊዜ ተመርጠው ጊዜያቸውን የጨረሱ አመራር አካላት ዳግም መመረጥ አይችሉም:: ሆኖም ግን ከአንድ ጊዜ እረፍት በኋላ ድጋም ሊመረጡ ይችላሉ፣

6) የምርጫውን ስነ-ስርዓት እንዲሳካ አግባብ ያለው ባለስልጣን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣

7) ለኮሚቴ አባልነት ምርጫ የሚወዳደሩ ዕጩ ተወዳዳሪዎች ለመምረጥ እንዲቻል በሚፈለጉ የኮሚቴ አባላት ብዛት ላይ በተጨማሪ እንደየ ኅብረት ሥራ ማህበራቱ ተጨባጭ ሁኔታ ዕጩዎች ተጠቁመው እንዲወዳደሩ ይደረጋል::

8) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ብዛት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪ ደንብ ውስጥ የሚወሰን ሆኖ ቁጥሩ የሚቋቋሙ የንዑሳን ኮሚቴ ዓይነትና ብዛት ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባል:: ሆኖም ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀ-መንበር ውጭ ሌሎቹ የአመራር ኮሚቴ አባላት የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ሰብሰቢ ሆነው ሊሰሩ ይችላሉ::

9. Taama miraacissa maroh ixxi 5—11 yakkem faxximta. Tahak amo gexewaay takkay immay inkih mododul ken dooran waqdi namma num amot keenih haan. Tohuuy balkih numuk teyni tu geek foxo raaqisaana gidi.

10. Luula taamah eglak amollai modod gexsan waqdi uddur akak tatre adoytit yenek deedala mari yenek ken foxot sinam doorak haan.

11. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 34(3 kee 6) madqeenim elle anuk awwalih mirocti akah doorimen udduruk qimbok xabba heenih sidocuk inki gaba qusba miroctit korta

12. Ta maasayyak 54(9) elle baxxaqimte innal nammey heele dooroh udduruk qimbisak qusubih dooren miroctit milaagime kal ciggiila 3[heele] dooroh uddur fan miraacinnal sugaanam duudan.

13. Gabak gabal tabsaanam takkeh gide wagiita doolat xagar banki sandug alfissi heeh, kalen maraa kee qusubih dooren marih fanat reeda tabsi 3 ayroh addat akah yakke innah absiisele. Wagiita doolat xagar qusubih dooren mara suge maraa kee taameynit elle tasseleeleqe ikkel wagiita doolat dagar tabsu abu xiqah.

9) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሚመሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ቁጥር ለውሳኔ አሰጣጥ አመቺ እንዲሆን ከ5 እስከ 11 አባላት መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም የሥራ አመራር ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ አማካኝነት ምርጫ ሲያካሄድ ሁለት ተጠባባቂ የሥራ አመራር ኮሚቴ ተመርጠው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የኮሚቴ አባላት በሚጓደልበት ወቅት የሚተኩ ይሆናል፡፡

10) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በየዓመቱ በሚያካሂደው ጉባዔ የሥራ ጊዜያቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተጓደሉ የኮሚቴ አባላትን ይተካል፡፡

11) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 34 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከቀድሞ የሥራ አመራር የኮሚቴ አባላት ከተመረጡበት ከሦስተኛ የሥራ ዘመን ጀምሮ ባለው የመጀመሪያ ዓመት ቢያንስ አንድ ሦስተኛው በአዲስ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ይተካሉ፡፡

12) በዚህ አንቀጽአንቀፅ 54 ንዑስ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ከሁለተኛው የምርጫ ዘመን የመጀመሪያ ዓመት ጀምሮ በአዲስ የተመርጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ሳይተኩ እስከሚቀጥለው ሦስተኛው የምርጫ ዘመን በአመራርነት ሊቆዩ ይችላሉ፡፡

13) እርክክቡ እስኪፈጸም ድረስ አግባብ ያለው ባለስልጣን የባንክ አካውንቱ እንዳይንቀሳቀስ በማድረግ በተሸናና በተመረጡ ኮሚቴ መካከል የስልጣን ርክክብ ሶስት ቀን ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ ሆኖም ነባሩና አዲስ የተመረጠው የሥራ አመራር ኮሚቴ አግባብ ያለው ባለስልጣን፣ ቁጥር ሠራተኞች እና አስመራጭ ኮሚቴ አባላት በታዛቢነት በተገኙበት የሥራ ርክክብ ሊያደርግ ይችላል፣

14. Raaqte mirocti qusba miroctih taamâ rorsah oyti yaceenim kee inki alsih addat taama kin yaybulleenimih qaaqa keenil tan.

15. Ummaan taama miraacissa marok taamah uddur sidiica liggida. Takkay immay amolladi modod elle yeemenek nammay heele addah doorimam duudah. Takkay ikkal inki num namma dooroh udduruk biso doorimam ma duuda

14) ነባር የኮሚቴ አመራር ለተተኪ የኮሚቴ አባላት ሥራዎች ያሉበትን ዝርዝር መረጃ የመስጠት እና ለአንድ ወር ሥራውን የማለማመድ ግዴታ አለባቸው፡፡

15) የማንኛው የሥራ አመራር ኮሚቴ የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሆኖ ጠቅላላ ጉባዔው ካመነበት ለሁለተኛ ጊዜ ሊመረጥ ይችላል፡፡ ሆኖም አንድ ሰው ከሁለት የሚርጫ ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

## 55) Taama miraacissa maroh adoytih taamaa kee qaaqa

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayak 35 madqimtem elle anuk umman taama miraacissa maroh adoyti ossotinah ciggilta abtoo kee qaaqa aallele
   a) Kulli luulâ taama waggittaamal egla awlisak malkitaah,gaaruwaah,ambalaalitte yagdube. Takkay immay ambalaalitte lakqol takkem tekkek amolladi modod edde xintal daffeysen tarmaanak tatre waytam faxximta.
   b) Luulâ taamah eglak cisab alhumitte (sanadwa) akah kibbimta innah aba.
   c) Ummaan eglâ culoola culô yoofental koboxtek waytam diggoysa elle tewqe inna lowsiisa
   d) Kulli alsal, kulli mafarril gaddaa kee kasaarah aybalaalaq ankacisa luulâ taamah eglak cisab qaafiyat diggoysa

## 55. የስራ አመራር ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ በተጨማሪነት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) በማንኛውም ጊዜ የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ወክሎ ይከሳል፣ ይከራከራል፣ ውሎችን ይዋዋላል፡፡ ሆኖም የሚያደርጋቸው ውሎችና ስምምነቶች በገንዘብ የሚሆን ከሆነ በመተዳደሪያ ደንባቸው በጠቅላላ ጉባዔ ከተቀመጠው የገንዘብ ጣሪያ በላይ ሊሆን አይገባም፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሂሳብ ሰነዶች እንዲሟሉ ያደርጋል፡፡

ሐ) ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገቢዎች በማህበሩ ገቢ ደረሰኝ ብቻ መሰብሰባቸውን ያረጋግጣል፤ አወጣጡን ይቆጣጠራል፤

መ) በየወሩ፣ በየሩብ ዓመቱ የሀብትና ዕዳ መግለጫ ሪፖርት ያዳምጣል፤ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ ጤናማነት ያረጋግጣል፡፡

e) Wagiita doolat xagar hinnay usuk akah idnise oxiter luulâ taamah eglah cisab akah fokkaaqa innah gita fiya

f) Taama miraacissa maro oxit gabbaaqul walalla itteh, amolladi mododuh akah xayyoowa innah gita fiya

g) Amolladi modod kee oxiter bahte gabbaaquk satqo beyak matteebannuu kee geeri xiinisso massos taamoomi aban

h) Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 26(4) tanim elle anuk edde xinti madqak ugutak qusubih hinnay qagitak xayyowta adoytiini assabalta fokkaaqak edde cabo xayyoysa

i) Adoyti idinil adoytiinuk yawqeenimih essero hirigak yargiqe. Takkay immay qellatal xiiriyan mara tekkek amolladi modod akah yargiqe innah xayyoysa

j) Luulâ taamah eglah adoytit edde xinti madqal elle enni itta gurral adoytit gar kee dirkik yawqeenik waytam digoysan

ሠ) አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም እሱ ውክልና በሰጠው የውጭ ኦዲተር አማካኝነት የኅብረት ሥራ ማህበሩ እንዲመረመር ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

ረ) የሥራ አመራር ኮሚቴ በኦዲት ሪፖርት ላይ በመወያየት ለጠቅላላ ጉባዔ እንዲቀርብ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

ሰ) የጠቅላላ ጉባዔ እና ኦዲተሩ ከሰጡት የሪፖርት ግብዓት በመውሰድ የቴክኒክ እና ሌሎች አስተዳደራዊ ማስተካከያዎችን ይወስዳል፣

ሸ) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ 985/2009 አንቀጽ 26 ንዑስ 4 ላይ የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የአዲስ ወይም የዳግም የአባልነት ማመልከቻ መርምሮ ውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፣

ቀ) በአባሉ ፈቃድ ከአባልነት የመሰናበት ጥያቄ ተቀብሎ ውሳኔ ይሰጣል፣ ሆኖም በጥፋት ለሚሰናበት የኅብረት ሥራ ማህበር አባል ውሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላላ ጉባኤ ያቀርባል፣

በ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባላት በመተዳደሪያ ደንብ ውስጥ በተገለፀው መልኩ መብትና ግዴታቸውን በአግባቡ እየተወጡ መሆናቸውን ያረጋግጣል፣

k) Luulâ taamah eglak edde xin madqak maysaasa edde xintak geeri miracsentitte wagiita doolat xagar bicseh yan edde xin qaguntak ugutak bicissi heeh amolladi mododuh xayyoysa, faaticiseenik geera taamal assa.

ተ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻያ፣ የውስጠ ደንብ ሌሎች መመሪያዎችን አግባብ ባለው ባለስልጣን በተዘጋጁ ረቂቅ ሞዴል መሠረት ያዘጋጃል፣ በጠቅላላ ጉባኤ አጸድቆ ስራ ላይ ያውላል::

l) Amolladi mododih edde cabooba yiysiisen edde xin madqooqi addâ xinto kee geeri yaysaqarroonuh esseran sanaditte wagiita xagaral xayyoysak yaysaqarren

ቸ) በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ የተሰጣቸውን የተሻሻሉ መተዳደሪያ ደንብ፣ የውስጠ ደንብ እና ሌሎች እንዲመዘገቡ የሚጠየቁ ሰነዶችን አግባብ ላለው ባለስልጣን በማቅረብ ያስመዘግባል፣

m) Wagiita doolat xagar yiysiisen maasayyooyi yukkuqeh, yayseqerrem yaysixxige waqdi taamal asisa

ነ) አግባብ ያለው ባለስልጣን የተሸሻሉ አንቀጾችን መቀበሉንና መመዝገቡን ሲያሳውቀው ሥራ ላይ ያውላል

n) Luulâ taamah eglah tuxiqle qusba abnitte cubbusak amolladi mododuh xayyoysak faaticiseenik geera abinal assa.

ኘ) ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሚጠቅሙ አዳዲስ አሰራሮችን በማጥናት፣ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ሲጸድቅ ስራ ላይ ያውላል::

o) Eylemma iyyen saami elle iyyen uddurul xaamimek waytam diggoysa adoytit xaamtuh koobaahisah. Tonnah ittallih lon envestimentih ossotina saami amolladi mododul faaticsisak yaylamme

አ) እንዲሸጥ የተወሰነውን ዕጣ በተያዘለት ጊዜ መሸጡን ያረጋግጣል፣ አባላት እንዲገዙ ያስተባብራል እንዲሁም ሊጋራ ኢንቨስትመንት የሚውል ተጨማሪ ዕጣ በጠቅላላ ጉባዔ አስወስኖ ይሸጣል::

p) Xaamite ossotinâ saami akah loowen madmal asekwaytam yasmite

ወ) የተሸጠው ተጨማሪ ዕጣ ሊታሰበለት ዓላማ እና ለአባላት ተጠቃሚነት ሥራ ላይ ማዋሉን ያረጋግጣል::

q) Taama miraacissa maro taama gexse tamlisaanam faxximtaamal sitta geenik amolladi mododul faxxiima baajet akah faaticisak qalala tamlisan kaadu xiiriyan

ከ) የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት የስራ አስኪያጅ አስፈላጊነት ላይ ስምምነት ከደረሱ የጠቅላላ ጉባዔው አስፈላጊውን በጀት ሲፈቀድለት አወዳድሮ ይቀጥራል፣ ያሰናብታል::

R) Luulâ taamah eglah edde xintaa kee adda xintoh madqak ugutak likaaci beyah adoytiitil fikiikisa, been abud waktil akah gacsan innah aba.

ዘ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ እና በውስጠ ደንብ መሰረት ይበደራል፣ ለአባላት ያሰራጫል፣ ብድርንም በወቅቱ እንዲመለስ ያደርጋል::

S/ Taama gexsee kee geeri taamah exxah abbobti sinni taama diggal gexsaanak waytam lowsiisah, kattaatah

ዠ) ሥራ አስኪያጅ እና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ሥራቸውን በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መወጣታቸውን ይከታተላል፣

T/ Edde xin kee adda xintoh madqaa kee geeri miracsentitteh adda fakoot adoytit kee miroctih axmaq geyoonu, barittoo kee aydakaakan yacee

ጠ) በመተዳደሪያ ደንብ፣ በውስጠ ደንብ፣ በሌሎች መመሪያዎች እና አሰራሮች ላይ ለአባላት እና ለአመራር አካላት ግንዛቤ እንዲፈጠር ትምህርት እና ስልጠና ይሰጣል::

U/ Adoytit saamii kee xoqoysi hinnay mago nagreyniitih tatrusa

ጨ) የአባላት ዕጣ እና ጥቅም ወይም ዕዳ ወራሽነታቸው በህግ ለተረጋገጠላቸው የአባል ወራሾች ያስተላልፋል፣

V/ Luulah eglaa kee adoyti fanat sittin way yoobokek idoola fan gexaanak afal ken bicsam gibbata.

የ) በኅብረት ሥራ ማህበሩና በአባላት መካከል አለመግባባት ሲኖር ወደ ሽምግልና ዳኝነት ከመሄዱ በፊት የሚያግባባ የመፍትሄ ሀሳብ ያፈላልጋል፣

W/ Luulâ taamah eglah miraccinni kukta, edde xinta, amolladi mododih edde caboobal yeceen abtoo kee qaaqak iroh aben taamah abreh gufte kasaarah, yekke qellatah cankah hinnay sittalluk esseriman.

ደ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ አመራር ኮሚቴ በአዋጅ፣ በመተዳደርያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውጭ በሚሰሩት ሥራ ምክንያት በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ በሚደርስ ኪሳራ ወይም ጥፋት ወይም ጉድለት በጋራ ወይም በግል ተጠያቂ ይሆናሉ::

X) Luulâ taamah eglal gufte kasaarah, esserima xagar cokmih xayyoysa agdaabe kattaata.

ጀ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ላይ በሚደርስ ጉዳት፣ ኪሳራ እና ጥፋት ያደረሱ አካላት ለህግ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፣

Y) Wagiita doolat xagar ruuba oxiterik kalah tan mihrat leelat cisab fokkaaqisen waqdi sanadal aban bicitte, oxiter taama kee qaaqaa kee miklal edde cabo tatrusa

ገ) አግባብ ካለው ባለስልጣን ውጭ ባሉ ኦዲተሮች ሂሳባቸውን ሲያስመረምሩ በሚደረጉ ስምምነት ሰነዶች ላይ የኦዲተሮች የስራ ኃላፊነት እና የክፍያ ሁኔታ ይወስናል፣

z) Luulâ taamah eglah edde xinti madqak ugutak ikoyta yaydarruh hinnay ikoyta yastaruh (kaluh) amolladi mododuh xayyoysak faaticisa

aa)xy) Geeri amolladi modod yacee taamoomi agdubele

2. Ta maasayyak (1) (a-t) tanim elle anuk ummaan luulâ taamah egla leh tan taamah caalataak ugutak ossotina taamaa kee qaaqa edde xintat haysitam duudah

3 Ummaan luulah egla ta maasayya (a-t) madqooqii kee issi edde xintal tan taamaa kee qaaqak iroh taamittam ma xiqta

## 56) Taama miraacissa maroh saqalih taamaa kee qaaqa

1 Luulâ taamah eglah saqal amolladi mododul saanih doorima, akah xiinam (amottinah kaat tanim) amolladi modod kee taama miraacissa maro.

2 Luulâ taamah eglaalik kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 35 madqimtem elle anuk taama miraacissa maroh saqal ciggilta taamoomi yagdube.

a) Amolladi modod, taama miraacissa maro hinnay borxi daffeyna qaaqal miraacisa

b) Cisab sanadittel, cheekil, nammahaytuh yafrime

ጸ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በመተዳደሪ ደንቡ መሰረት ንብረት ለማፍራት ወይም ንብረት ለማስወገድ ለጠቅላላ ጉባኤ አቅርቦ ያጸድቃል፣

ፀ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ጠ) ያሉት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ ባህሪውን መሰረት በማድረግ ተጨማሪ ተግባርና ሃላፊነቱን በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ሊያስቀምጥ ይችላል፣

3) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ጠ) ድንጋጌ እና በራሱ መተዳደሪ ደንብ ከተቀመጠው ተግባርና ሃላፊነት ውጭ መስራት አይችልም፣

## 56. የሥራ አመራር ኮሚቴ ሊቀ መንበር ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀ-መንበር በጠቅላላ ጉባዔ አባላት በቀጥታ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤ እና ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፡፡

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀ-መንበር የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፣

ሀ) የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ ስብሰባን በኃላፊነት ይመራል፣

ለ) የሂሳብ ሰነዶች እና ቼክ ላይ በጣምራ ይፈርማል፣

c) Luulâ taamah eglah migaaqal malkitimah, malkitah hinnay gacsa aba

d) Luulâ taamah egelah migaaqal ambalal aba hinnay yacee

e) Geeri edde xin madqah addal tan taamoomii kee qaaqa le tonnaah amolladi modod edde cabooba abinal asisa

## 57) Taama miraacissa marok ciggiila saqalih taamaa kee qaaqa

1 Luulâ taamah eglak c/saqal amolladi mododul doorima. Akah xiinam taama miraacissa maro. (amottinah kaak tanim) taama miraacissa maro

2 Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 35 kee 46 (1) madqimtem elle anuk marok c/saqal ciggilta abtootaa kee qaaqa aallele

a) Saqal deedala waqdi kay foxok taamita, egla miraacisa

b) Kulli taama miraacissa maroh adoytit innaah edde xinti madqa elle enni itta gural nali marokteynah kobxise akkuk qaaqak awqele

c) Luulâ taamah eglak taama miraacissa maro kaah acayinnan taama ossotinah abele.

ሐ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ይከሳል፣ ይከሰሳል ወይም መልስ ይሰጣል፣

መ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ ስም ውል ይዋዋላል፣

ሠ) ሌሎች በመተዳደሪያ ደንብ የሚወሰኑ ተግባርና ኃላፊነት እና ከጠቅላላ ጉባኤ የሚሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፣

## 57. የሥራ አመራር ኮሚቴ ምክትል ሊቀ መንበር ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ምክትል ሊቀ-መንበር በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 35 እና በዚህ አንቀጽአንቀፅ 46 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ አመራር ኮሚቴው ሊቀ-መንበር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣

ሀ) ሊቀ-መንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ሊቀ-መንበሩን ተክቶ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ስራ ይመራል:: 52

ለ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል::

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ሥራዎች ደርቦ ይሰራል፣

## 58. Taama miraacissa marok kutbe abeyni taamaa kee qaaqa

1 Luulâ taamah eglak taama miraacissa maroh kutbe abeyni amolladi mododul doorima, taama miraacissa maroh gubat raaqa (taama miraacissa maro amottinah kaak tan)

2 Eglak kutbe abeyni dooro amolladi mododul takke amogacsi kaak taama miraacissa maro akkuk ciggilta taama kee qaaqa aallele

a) Eglak saqala illuk gacak (malisak) kobox ajanxa bicisa, geeri maroh adoytiitik ajanxa yaskatte
b) Kobox seeco kee ajanxa adoytiitih ruuba guftem yasmite
c) Amolladi modod kee taama miraacissa maroh guuma yabbixe bicsah
d) Eglak baxaabaxsa le kutbe taamoomi aba
e) Tamlisen taameynit aalle wayta eglaalik muhri, guuma, maysaqarra kee sanadwa meqennal yabbixe luulâ taamah eglah biiro missoysa edde xinti madqa elle ittannal
f) Taama miraacissa maroh adoyti ossotinah inki nali maroh mirac akkuk issi qaaqak yawqem faxximta.
g) Luulâ taamah egla kaah tacee geeri taamoomi abele

## 58. የሥራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፀሐፊ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ፀሐፊ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡፡

ሀ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ሊቀመንበር ጋር በመመካከር የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ከሌሎች የኮሚቴ አባላቶችም አጀንዳዎችን ይሰበሳባል፣
ለ) የስብሰባው ጥሪዎችንና አጀንዳዎች ለአባላት ይልካል፣ መድረሱን ያረጋግጣል፣
ሐ) የጠቅላላ ጉባኤ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ይይዛል፤ ያዘጋጃል፣
መ) የተለያዩ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የጽህፈት ሥራዎችን ያከናውናል፣
ሠ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበሩን ማህተም፣ ቃለ-ጉባኤ፣ መዛግብትና ሰነዶችን በአግባቡ ይይዛል፤ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ጽ/ቤትና ቢሮ ያደራጃል፣
ረ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣
ሰ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ሥራዎች ደርቦ ይሰራል፡፡

Afar National Language Culture History Research Center

## 59) Taama miraacissa marok lakqo yabbixi abtoo kee qaaqa

1 Taama miraacissa marok lakqo yabbixi amolladi mododul doorima amo amottabi kaak taama miraacisa maro

2 Lakqo yabbixi amolladi mododul doorimak amo elle kaak gactam taama miraacissa maro toh luk ciggilta taamoomi aalle le.

a) Tamlô taameynit aalle wayta eglaalik culenta yoofental kobxisa.

b) Tamlisen taameynit aalle wayta eglaalik taamah faxximta awqenta saqal warkatah amriseeh, eglak awqenti amrih sanadal faaticimtem meklah.

c) Luulâ taamah eglak lakqo yabbixi taama miraacissa maroh adoyta akkuk tamlisen lakqo yabbixi kulli ayro abah yan taama kaak kattaatah, taama missat abek waytam kaa kattaatah

d) Lakqo yabbixi umman eglâ maaluu kee sanad dacrisa

e) Awqentaa kee culenti yan waqdi wohim qokolta sanadwa tanim diggoysa

## 59. የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ ተግባርና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) ገንዘብ ያዥ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበራት ገቢዎችን በገቢ ደረሰኝ ይሰበስባል፣ 53

ለ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው ኅብረት ሥራ ማህበራት ለሥራ የሚያስፈልግ ወጪዎችን በሊቀመንበሩ በደብዳቤ ሲታዘዝና በማህበሩ የወጪ ማዘዣ ሰነድ ሲጸድቅለት ይከፍላል፣

ሐ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ገንዘብ ያዥ የኮሚቴ አባል የተቀጣሪ ገንዘብ ያዥ የየዕለቱን ሥራ በቅርበት በተሰጠው የሥራ ድርሻ ዝርዝር መሰረት መስራቱን ይከታተላል::

መ) ኅብረት ሥራ ማህበር ማንኛውንም የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብና ሰነዶችን ይጠብቃል፣

ሠ) በወጪና በገቢ ሂደት ወቅት የወጪና የገቢ ደጋፊ ሰነዶች መኖራቸውን ያረጋግጣል፣

f) Luula taamah eglak cisab qexso edde xinti madqa elle itta innal kee geeri miracsenti elle iyya innal gexsittak waytem yasmiteemih dirk kaal tan.

g) Tamlisen taameynit aalle wayta luulah eglaalih eglak cisab sanadwa chekwah bagul saqalluk gacca iyyah fermo daffeysa

h) Ummaan taama miraacissa maroh adoytih innaah nali maroh gaaboyse akkuk issi qaaqak awqele

i) Luulah eglak taama miraacissa maro tacee ossotina taama abele

3 Luulâ taamah eglak, taama miraacissa maroh lakqo yabbixi takkem maali abbaxal yayse abak raag leeh, meqem kabanal yamixxigeeh, adoytit garil makkaqa le num takkem faxximta.

## 60. Cisab reedantih abtoo kee qaaqa

1. Tamlisen cisab mihrat le aalle wayta luulah eglak cisab reedanti amolladi mododul doorima. Amottabi kaak taama miraacissa maro kinnuk ossotinah ciggilta abtootaa kee qaaqa aallele.
   a) Luulah eglak cisab missat bicsaah, kattaatah

ረ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ አሰራር በመተዳደሪያ ደንብ፣ በውስጠ ደንብ እና በሌሎች መመሪያዎች መሰረት መከናወኑን የመፈጸም ግዴታ አለበት፣

ሰ) የቅጥር ሰራተኞች በሌላቸው የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሂሳብ ሰነዶች፣ በባንክ ቼኮች ላይ ከሊቀመንበሩ ጋር በጋራ ይፈርማል፣

ሸ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣

ቀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፣

3) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ገንዘብ ያዥ ሆነው የሚመረጡት በገንዘብ አያያዝ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ እንዲሁም በስነምግባራቸው በአባላት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

## 60. የሂሳብ ሹም ተግባርና ኃላፊነት

1) ቅጥር ሂሳብ ባለሙያ በሌለበት የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሂሳብ ሹም በጠቅላላ ጉባዔ አባላት የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ሂሳብ በትክክል ያዘጋጃል፣ ይከታተላል፣

Qafar ... /Ra/DO Qafar Afaay Qaadaa kee Ad... Culture ... Research Center

b) Luulâ taamah eglak maytanni kee tangayye ikoyta, abud, kappitala, culoo kee awqenta amotlih yaysaqarreh daffeysa
c) Cisab maysaqarra, kee geeri cisab sanaditte dacrisah
d) Kulli awqenti missat amriseenik waytam diggoysa
e) Eglak faynansi gabbaaqu, alsi cisab gabbaaqu, cisab alfimek 3-5 ayroh addat taama miraacissa maroh xayyoysa.
f) Lakqo yabbixxi illuk xaynal taamitak, egla maali akah daccarsima innah abele.
g) Saqal kee lakqo yabbixxi illuk cisab sanadwa kee chekil yafrime.
h) Tamlisen cisab taameyni kaah yeceen taama missah abak waytam kattaata.
i) Ummaan taama miraacissa maroh adoyti akah aba innah geeri nali maroh gaaboyse akkuk taamitele edde xin madqa elle itta innal.
j) Ossotinah taama miraacissa maro kaah tacee taamoomi abele.

2. Luulâ taamah eglak cisab reedantuh doorima num cisab abbaxal yayse abak raag le num takkem faxximta.

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረት፣ ብድር፣ ካፒታል፣ ገቢና ወጪ ሙሉ በሙሉ መዝግቦ ያስቀምጣል፣

ሐ) የሂሳብ መዝገቦችና ሌሎች የሂሳብ ሰነዶች ይጠብቃል፣

መ) ማንኛውም ወጪ በትክክል መታዘዙን ያረጋግጣል፣

ሠ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የፋይናንስ ሪፖርት ወርሀዊ የሂሳብ ሪፖርት በተዘጋ ከ3 እስከ 5 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፣

ረ) ከገንዘብ ያዥ ጋር በቅርበት በመስራት የኅብረት ሥራ ማህበሩን ገንዘብ በአግባቡ እንዲጠበቅ ያደርጋል፣ 54

ሰ) ከሊቀመንበሩ እና ከገንዘብ ያዥ ጋር በመሆን በጣምራ በሂሳብ ሰነዶችና በቼክ ላይ ይፈርማል፣

ሸ) የተቀጣሪ ሂሳብ ሰራተኛ የየዕለቱን ሥራ በተሰጠው ዝርዝር የሥራ ድርሻ መሰረት መስራቱን ይከታተላል::

ቀ) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሰቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል፣

በ) የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል::

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የሂሳብ ሹም ሆነው የሚመረጡት በሂሳብ አያያዝ የተሻለ ልምድና ተሞክሮ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፣

3. Luulâ taamah eglak cisab sanadwa wagiitah yan doolat xagar elle yascasse gital yabbixeenim faxximta
4. Luulâ taamah eglaalih cisab alfimeek geera sissikuk cisab maysaqarra, tirfii kee kasaara, gaddaa kee mago kee geeri cisab maybalaalaqa bicsaanam faxximta

## 61) Geeri taama miraacissa maroh adoytit

1. Luulâ taamah eglak taama miraccissa marok geeri adoytit amolladi modod ken dooraah, amottabi keenik taama miraacissa maro akkele
2. Ummaan taama miraacissa maroh abtootaa kee edde cabob missah yangalen missah tan xogolo lon
3. Ummaan taama miraacissa maroh adoytit akah lennaah edde xintal tan ossotina taamak geeri nali maro miraacisan.
4. Geeri taama miraacissa maro keenih tacee taamoomi abelon.

## 62. Lowsis maroh adoytih dooroh magdo, amottabeyna wagittaama

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 36 elle ta innal anuk luulâ taamah eglak lowsis maroh adoytit dooro, magdo, amo elle gacseyna, taamah uddur wagsiisak ossotinah ciggiltam aallele.

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሂሳብ ሰነዶችን እና ሌሎች መዛግብትን አግባብ ያለው ባለስልጠና በሚመራው መንገድ መያዝ አለበት፣

4) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ከተዘጋ በኋላ በተቻለ ፍጥነት የሂሳብ መዛግብት፣ ትርፍ እና ኪሳራ ሂሳብ፣ ሀብትና ዕዳ እና ሌሎች የሂሳብ መግለጫዎችን በየጊዜው ማዘጋጀት አለበት።

## 61. ሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጡ ሲሆን ተጠሪነታቸው ለኅብረት ሥራ ማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ነው፣

2) በማንኛውም የሥራ አመራር ኮሚቴ ተግባራት እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ከሌሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት በእኩል የመሳተፍ ድምፅ አላቸው።

3) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባል በተጨማሪ በመተዳደሪያ ደንብ በሚወሰነው መሠረት የአንድ ንዑስ ኮሚቴ ሰብሳቢ ሆኖ ኃላፊነቱን ይወጣል።

4) በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።

## 62. የቁጥጥር ኮሚቴ አባል ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 36 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት እና የሥራ ዘመን ላይ በተጨማሪነት የሚከተሉት ያካትታል፤

a) Lowsis maroh adoytit luulah eglah adoytit yakkeenim faxximta

b) Luulâ tamah eglah edde xintal tan adoytit dirki kibam faxximta

c) Kaah yeceen qaaqa meqennal yagdubeeh, sinaamat bicak taamitaa num takkemi

d) Meqem kaban le num takkeemi

e) Tahak afal qamal umaanel, aamanti sinnâ baatilih malkitime num akke waytay

2. Ken edde xin madqal amolladi mododul amottinah lowsis maro aallele

3. Ummaan luulâ taamah egla 3-5 yakke adoytit le lowsis maro aallele

4. Cubewayni sababah adoytiinuk yawaquwaa adoytih foxok culuwa inki adoyta naharal elle amolladi mododul dooranam bicta.

5. Lowsis maro miracaay, kutbe abe kee adoyta aalle le .

ሀ) የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ለ) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደርያ ደንብ ውስጥ የተጠቀሱትን የአባልነት ግዴታዎች በብቃት የሚወጣ፣

ሐ) የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ተግባብቶ እና ተባብሮ በመስራት መወጣት የሚችል፣

መ) መልካም ስነ-ምግባርና ተቆርቋሪነት ያለው፣

ሠ) ቀደም ሲል በምግባረ ብልሹነት ወይም በእምነት ማጉደል ወንጀል ክስ የሌለበት፣

2) በመተዳደሪያ ደንባቸው ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤ የሆነ የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

3) ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር 3 ወይም 5 አባላት ያሉት የቁጥጥር ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡

4) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከኃላፊነታቸው የሚለቁ አባላትን የሚተካ ተጠባባቂ አንድ የኮሚቴ አባል በጠቅላላ ጉባዔ ማስመረጥ ይቻላል፡፡

5) የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባል ይኖሩታል፣

## 63. Lowsis maroh abtoo kee qaaqa

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayya 37 tanim elle anuk ummaan luulâ taamah eglah lowsis maro ossotinah ciggilta abtoo kee qaaqa aallele

## 63. የቁጥጥር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 37 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ በተጨማሪነት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ያካትታል፤

a) Luulâ taamah egla wagitta caagiidal lowsis maroh kuboxul ajanxah ugusak caagid fokkaaqan. Massoyseh meqe edde cabol qangarah hinnay kutbeh taama miraacissa maroh yaysixxigen

b) Taama gexsee kee taamah exxaaxih abbobti qaaqak yawqeenik waytam kattaatan

c) Taama miraacissa maro baxaabaxsa le xagooralluk aban ambalal kee tubicitte amolladi modod edde cabok ugutak tekkek waytam yasmite

2. Aamanti le cisab kee luulah eglah ikoytaa kee magooga meqe gurral aysaqarruk akah daffeysan innah aban

## 64) Luulâ taamah eglak lowsis maroh gaaboyseh abtoo kee qaaqa

1. Luulah eglak lowsis maroh gaaboyse amolladi marol doorima, amo elle kaak taduurem amolladi mododo keek lowsis maro.

2. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 37 kee ta maasayyak 53(1) madqeenim elle anuk lowsis maroh gaaboyse ciggilta abtoo kee qaaqa aalle le

   a) Taama miraacissa maroh daffeynat geytimak xongolo aalle kal mabla yaceeh. Edde caboh takke mabla yaceeh

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች በቁጥጥር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በአጀንዳ መልክ በማንሳት ጉዳዩን ይመረምራል፤ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው የውሳኔ ሃሳብ በቃል ወይም በጽሁፍ ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያሳውቃል፡፡

ለ) ስራ አስኪያጅ እና የሥራ ክፍል ኃላፊዎች ሥራቸውን በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መወጣታቸውን ይከታተላል፤

ሐ) የሥራ አመራር ኮሚቴ ከተለያዩ አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን ውሎችና ስምምነቶች በጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔና በመተዳደሪያ ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

2) ተዓማኒና ትክክለኛ ሂሳቦች እና የህብረት ሥራ ማህበሩ ንብረቶች እና እዳዎች ትክክለኛ መዝገብ እንዲይዝ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ;

## 64. የኅብረት ሥራ ማህበር የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ ተግባር እና ኃላፊነት

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ በጠቅላላ ጉባዔ አባላት በቀጥታ የሚመረጥ ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባኤ እና ለቁጥጥር ኮሚቴ ነው፤

2) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 37 እና በዚህ አንቀጽአንቀፅ 53 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የቁጥጥር ኮሚቴ ሰብሳቢ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፤

ሀ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ያለድምፅ የውሳኔ ሃሳቦችን ይሰጣል፤

b) Egla wagitta caagiida taama miraacissa maroh daffeynal ajanxa takke innah aba

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ አጀንዳ ሆነው እንዲነሱ ጥረት ያደርጋል፡፡

c) Taama miraacissa maroh daffeynal ugsah yan malooli yayqarreenih

ሐ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚያነሳቸው ሃሳቦች በቃለ-ጉባኤ መዝገብ ላይ ይመዘገባሉ፣

d) Taama miraacissa maroh daffeynal ugutte ajanxaa kee edde cabeenim gabbaaqu lowsis maroh gaaboynal gabbaaqah

መ) በስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የተነሱ አጀንዳዎች እና የተደረሰባቸውን ውሳኔዎች ሪፖርት በቁጥጥር ኮሚቴ መደበኛ ስብሰባዎች ላይ ለሌሎች የቁጥጥር ኮሚቴ አባላት ያቀርባል፣

e) Lowsis maro katattam faxximta taamoomih taddiira ayyaaquk kattaatah. Lowsis aba, tambulle boohaahi tenek taama miraacissa maroh afah kee kutbeh warsa yaysixxige

ሠ) የቁጥጥር ኮሚቴ ክትትል ሊደረግባቸው የሚገባቸውን ሥራዎች ፕሮግራም በማውጣት ክትትልና ቁጥጥር ያደረጋል፤ የታዩ ክፍተቶች ለስራ አመራር ኮሚቴ በቃልና በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

f) Geeri amolladi modod kattaata akak iyye ossotina taamoomi abele

ረ) ሌሎች በጠቅላላ ጉባዔ ክትትል እንዲያደርግ የተሰጠውን ተጨማሪ ሥራ ያከናውናል፡፡

## 65) Geeri nali maroorak adoytit dooroh magdo, amottiniinu

## 65. ስለሌሎች የንዑሳን ኮሚቴ አባላት ምርጫ መስፈርት፣ ተጠሪነት

1. Luulâ taama eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayya 38 tanim elle anuk umman luulâ taamah eglak nali maroora ossotinah ciggilta maqdooda aalle le.

1) በኅብረት ሥራ ማበራት አዋጅ ቁጥር 985/2009 አንቀፅ 38 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የንዑሳን ኮሚቴዎች በተጨማሪነት የሚከተሉትን መስፈርት ያካትታል፤

a) Nali maroh adoytit eglah adoytiitiy adoytiini dirki kibta yakkeenimi

ሀ) የንዑሳን ኮሚቴዎች አባላት የኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል የሆኑና የአባልነት ግዴታቸውን የሚወጡ፣

b) Elle yeceen qaaqa sinam lih bica num tikki iyyeh cattiimak taamituh bicsite

ለ) የተሰጠውን ኃላፊነት ተግባብቶ እና ተባብሮ ለመስራት ዝግጁ የሆነ፣

c) Sinam catuh kaxxa fayxi leeh, caalat meqe num yakkem

d) Edde doorime maroh caagidik axmaq leeh, abak raag lem faxximta

e) Dagnal yaktubeh yakriye num yakkeemi

2. Luulah eglaali xissa nali maroora ken eglah qaynat kee caalat elle faxah yan innal sinni edde xintak uguta xissimtaama

3. Ummaan luulah taamah eglak taama miraacissa maroh adoytit saqalak kalih mari inkih nali maroh gaaboyseenitih yanin

4. Luulâ taamah eglak edde xintak ugutak xissimta nali maro, 3 matamagga

5. Kulli nali maro kutbe abe kee gaaboyse kee adoyta le

6. Luulah eglah edde xintat cubeween sababah taama cabta adoytiitih foxok culsoonuwaan inki maroh adoyta amolladi mododul dorsiisaanam duudaanah.

7. Cubewaak sugen sababah nali maroh adoyti katek, naharal elle foxo qambaaleh dooren adoyti foxot sugam dibuk inki doorah udduru

## 66) Nali maroh reeda kee abto

1. Ummaan luula taamah eglak nali maroora ken edde xintih madqal elle tan ennal anuk ciggilta abtootaa kee qaaqa aalle lon

ሐ) ሰዎችን ለመርዳት ፅኑ ፍላጎትና መልካም ስነ-ምግባር ያለው፤

መ) በተመረጠበት የንዑስ ኮሚቴ ውስጥ በቂ ግንዛቤና ልምድ ያለው፤

ሠ) ቢያንስ ማንበብና መፃፍ የሚችል፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚያቋቁሟቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች እንደየኅብረት ሥራ ማህበራቱ ዓይነትና ባህሪያት እንዲሁም በመተዳደሪያ ደንባቸው በሚወሰኑት መሠረት ይሆናል፡፡

3) በማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት ሊቀ-መንበሩን ሳይጨምር የእያንዳንዱ የንዑሳን ኮሚቴ ሰብሳቢዎች ይሆናሉ፡፡

4) ማንኛውም የንዑሳን ኮሚቴ አባላት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሠረት ቁጥራቸው ከ 3 ያልበለጡ የተለያዩ ተግባርና ኃላፊነት ያላቸው ንዑሳን ኮሚቴዎች ይኖሩታል፤

5) እያንዳንዱ የንዑሳን ኮሚቴዎች ሰብሳቢ፣ ፀሐፊና አባል ይኖሩታል፤

6) በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከኃላፊነታቸው የሚለቁ አባላትን የሚተካ ተጠባባቂ አንድ የኮሚቴ አባል በጠቅላላ ጉባዔ ማስመረጥ ይቻላል፡፡

7) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የንዑስ ኮሚቴ አባላት ሲጓደሉ በተጠባባቂነት የተመረጠ ማንኛውም ግለሰብ ሊታካ የሚችለው ለአንድ የምርጫ ዘመን ብቻ ይሆናል፡፡

## 66. የንዑሳን ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር

1) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የንዑሳን ኮሚቴዎች በመተዳደሪያ ደንባቸው የሚወሰኑት እንደተጠበቀ ሆኖ በዋናነት የሚከተሉትን ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፤

a) Edde xintaa kee adda xintol nali maroorah tomcowwe abtootaa kee qaaqa yagduben

b) Luulâ taamah eglak nali maroh ekraaro bicsan, taama miraacissa maroh gabat faaticisan.

c) Ekraarok ugutak taamâ taddiiraa kee raatibik yan koboxuh uddur yargiqeen

d) Nali marok taamâ loftil tontocowwi taama miraacissa maroh mablooli kee taama miracsentittel walalak abinal asisan

e) Nali marok taamah angagoyyaa kee garayteh tan gibdaabinitte taama miraacisse maroh gabbaaqu xayyoysan

f) Nali maroh daffeynaanil ugutta takkusaasi, nali maroh guuma yaysaqarren

g) Geeri taama miraacissa maroh adoytit tacee taamoomi ossotinah abelon

2. Luulâ taamah eglak taamâ qamal kee taamâ baarissok ugutak, taama miraacissa maroh adoytit kulli nali maroh miraacih yanin

ሀ) በመተዳደሪያ ደንቡና በውስጠ ደንብ ውስጥ ለንዑስ ኮሚቴው የተሠጡትን ተግባርና ኃላፊነት ያከናውናል፡፡

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የንዑስ ኮሚቴ የሥራ ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለስራ አመራር ኮሚቴ ያጸድቃል፡፡

ሐ) በዕቅዱ መሠረት የሥራው መርሃ ግብር እና የመደበኛ ስብሰባ ጊዜው ይወስናል፤ ለስራ አመራር ኮሚቴ ያሳውቃል፡፡

መ) በንዑስ ኮሚቴው የሥራ ድርሻ ላይ የተሰጡ የሥራ አመራር ኮሚቴ አስተያየቶችን እና የሥራ መመሪያዎችን በመወያየት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

ሠ) የንዑስ ኮሚቴውን የሥራ እንቅስቃሴና ያጋጠሙ ማነቆዎችን ለስራ አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

ረ) በንዑስ ኮሚቴ ስብሰባዎች ላይ የሚነሱ ሃሳቦች በንዑስ ኮሚቴው ቃለ-ጉባኤ መዝገብ ላይ ይመዘገባል፣

ሰ) ሌሎች በስራ አመራር ኮሚቴ አባላት የሚሰጡ ስራዎችን በተጨማሪነት ያከናውናል፡፡

2) እንደ ኅብረት ሥራ ማህበሩ ሥራ ባህሪና የሥራ ስፋት የሥራ አመራር ኮሚቴ አባላት እያንንዳቸው የንዑሳን ኮሚቴዎችን በሰብሳቢነት ይመራሉ፣

## 67) Taama miraacissa maro hinnay lowsis maro hinnay nali maroh adoytitik qaaqak elle diiriyan gurra

1. Ummaan maroh doorime adoyti cubewayni sabab kaat boodek adoytiinuh cabam faxek taama miraacissa hinnay lowsis maro hinnay nali maroh assabalta xayyoysam faxximta.
2. Taama miraacissa hinnay lowsis maro hinnay nali maro essero edde xayyoysen 30 ayroh addat kutbeh xayyoysaanam faxximta
3. Ummaan maroh adoyti luulah eglah edde xinta sadda taamat asek amottinah kaak tan taama miraacissa maro hinnay lowsis maro hinnay nali marok solo kaat gacak amolladi mododuh edde caboh xayyowele
4. Deedala adoyti yenek akah deedalam asmatuk afal elle dooren foxo qambale edde cula woo foxot
5. Foxot culak taamitak suge adoyti hinnay foxo qambaale aallewaa kee qusubih doorimam faxximek liggidi raatib daffaynal taama gabbaaqi xayyoowak qusuba maroh adoyti akah doorima innah aba.
6. Inki maroh adoyti sittalakleh 3 daffeynak raaqek issi labbataak cabe num diqsitaah foxo qambaale kay foxot culsan.

## 67. የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ አባላትን ከኃላፊነት ስለመሰናበት

1) ማንኛውም የኮሚቴ ተመራጭ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሲያጋጥመው ከኮሚቴ አባልነት ለመሰናበት ከፈለገ ለሥራ አመራር ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፣

2) የሥራ አመራር ወይም የቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ጥያቄው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ በጹሁፍ መልስ መስጠት ይኖርበታል፣

3) ማንኛውም የኮሚቴ ተመራጭ የኀብረት ሥራ ማህበሩን ደንብ የሚጻረር ደርጊት ከፈጸመ ተጠሪ በሆነበት በሥራ አመራር ወይም በቁጥጥር ኮሚቴ ወይም በንዑስ ኮሚቴ ከሥራው ታግዶ ለጠቅላላ ጉባዔ ቀርቦ ውሳኔ እንዲቀርብ ይደረጋል::

4) የተጓደሉ የኮሚቴ አባል የተጓደለበትን ምክንያት እና ቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ ምርጫ በተጠባባቂነት ከተመረጡ የኮሚቴ አባላት ይተካል::

5) በተተኪነት ሲሰሩ የቆዩትን የኮሚቴ አባላት ወይም ቀድሞ ተተኪ የሌለውና አዲስ ሊመረጥ የሚገባው ከሆነ በዓመታዊ የመደበኛ ስብሰባ የሥራ ሪፖርት ይቀርባል አዲስ የኮሚቴ አባል እንዲመረጥ ያደርጋል::

6) አንድ የኮሚቴ አባል ካለ በቂ ምክንያት ለሦስት ተከታታይ ጊዜ ካልተገኘ ከኮሚቴ አባልነቱ በራሱ ፈቃድ እንደተሰናበተ ተቆጥሮ በቦታው በተጠባባቂነት ቀድሞ በጠቅላላ ጉባኤ በተመረጡ አባላት የሚተካ ይሆናል:: የጠቅላላ ጉባኤ እንዲያውቀው ይደረጋል::

7. Taama miraacissa maro hinnay lowsis maro hinnay nali maro foxo teelleeh woo foxot gaca foxo qambaale ane wayya heek amollodi modod qambaale kal adoytiitik nagay yangayye num elle sugah awlisak tamsiisaanam xiqqimtah, takkay immay inki liggidak biso awliinol taamitam ma duuda

8. Cubewaak sugen caalat yoobokeemih taagah awlisen adoytih caagid amolladi modod akah yaaxige innah aban elle awlisan gurri edde xintal yan.

## 68. Taama gexse elle tamlisan inna, kay abtoo kee qaaqa

1. Luulâ taamah eglaalih kuktih ixximak 985/2009 maasayyak 39 tanim anuk ummaan luulâ taamah eglah taama gexse ciggilta abtoota ossotinah le

a) Amolladi modod kee taama miraacissa maroh amrik ugutak luula taamah eglak istraatejik ekraaroo kee bajet qagunta bicsah.

b) Ekraaro amolladi mododul faaticisimteek geera kah yibbixxen waktii kee bajetit yagdube.

c) Abuwaa taamoomi edde xinti madqaa kee taama rooroh addat haysiisa

d) Amolladi modod bajet idnissek ixxiga lee xiqto le mihrat leela tamlisa

7) የተጓደሉ የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቁጥጥር ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ከተጠባባቂ አባለት ተክቶ ማሰራት የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ወይም የሚተካ ሰው የማይኖር ሆኖ ሲገኝ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሳይጠበቅ ከአባላት ውስጥ የተሻለ እንቅስቃሴ ያለውን በጊዜያዊነት ወክሎ ሊያሰራ ይችላል:: ሆኖም ከአንድ አመት በላይ ተወክሎ መስራት አይቻልም::

8) ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከአባላት መካከል ስለተወከለው አባል የጠቅላላ ጉባኤ እንዲያውቀው ይደረጋል:: ስለ አወካከሉ በመተዳደሪያ ደንባቸው ውስጥ የሚገለጽ ይሆናል፣

## 68. የስራ አስኪያጅ አቀጣጠር፣ ተግባርና ኃላፊነት

1) በኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር አንቀፅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር ስራ አስኪያጅ በተጨማሪ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፤

ሀ) በጠቅላላ ጉባዔ እና የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጠውን አመራር መሠረት በማድረግ የኅብረት ሥራ ማህበሩን ረቂቅ ስትራቴጂክ ዕቅድና በጀት እንዲሁም ዓመታዊ ዕቅድ ያዘጋጃል::

ለ) ዕቅዱ በጠቅላላ ጉባዔ ሲጸድቅ በተያዘለት ጊዜና በጀት ይፈፅማል:: ያስፈፅማል::

ሐ) የሚያከናውናቸው ተግባራት በመተዳደሪያ ደንብ እና በስራ ዝርዝር ውስጥ እንዲካተት ያደርጋል፣

መ) በጠቅላላ ጉባዔ በጀት ሲፈቀድለት በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች ይቀጥራል፣

e) Tamliseh yan taameynit bicsah yan taama rorsak ugutak sinni qaaqak yawqeenik waytam yasmiteh

f) Luulah eglah farmok ugutak meqem kaban qamalih miracsenta bicisak abinal akah assan innah aba

g) Taama miraacissa maroh addal xongolo maleh yangaleh, mihratli acayuk yen maybalaalaqa yacee

h) Luulah taamah eglah adoytiitih fanat xoqoysi sittin way culaamak meqe abni siirat fidsele mihrat qokol abele

i) Aamanti le wakti oytittey aggiriqqe sinni wagiitah yan xagarah tatrusaamih dirki kaal tan.

j) Amolladi mododul xayyowwe iroo kee adda ooxitih gabbaaquk mablooli gaaboysak massos faxxam akah massoyta innah aba.

k) Luulâ taamah eglah adoytit akke waa marat aba angaaraw baxsa le gurral oytih yabbixem faxximta

l) Adoyti yiimi (yiikoyta) akah itta innah ekraarisa taamita

m) Yayse angagoyya abte adoytit akah ilsitta innah gita bicisak mabla miraacissa maroh xayyoysa idnisan waqdi taamal asisa

n) Istiratejik abtootah agdaabe, faynansi maqar kee xiinissoh abtoota aamanti le gurral kutbeh adoytiitih inkih akah gufta innah absiisa

ሠ) የቀጠራቸው ባለሙያዎች በሚያዘጋጀው የስራ ዝርዝር መሠረት ኃላፊታቸውን እየተወጡ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

ረ) ከኅብረት ሥራ ማህበሩ ተልዕኮ አንፃር የሥነ-ምግባር ባህሪያት መመሪያ በማዘጋጀት ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፣

ሰ) የስራ አመራር ኮሚቴ ስብሰባ ላይ ያለ ድምፅ በመሳተፍ ሙያዊ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

ሸ) በኅብረት ሥራ ማህበር አባላት መካከል የጥቅም ግጭት ሊያስነሱ የሚችሉ ጉዳዮች አሰራር እንዲዘረጋ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

ቀ) ወቅታዊ፣ አስተማማኝና ተከታታይነት ያለው መረጃ ለሚመለከታቸው አካላት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

በ) የጠቅላላ ጉባዔ ላይ የቀረቡ የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖርት አስተያየቶችን በማሰባሰብ ቀጣይ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ያደርጋል፡፡

ተ) ኅብረት ሥራ ማህበሩ አባል ካልሆኑ ሌሎች አካላት ጋር የሚያደርጋቸውን የሥራ እንቅስቃሴ በተለየ ሁኔታ መረጃ መያዝ ይጠበቅበታል፣

ቸ) የአባላትን የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድጉ ተግባራትን አቅዶ መስራት ይኖርበታል፣

ነ) የተሻለ ተሳትፎ ላደረጉ አባላት ማበረታቻ የሚያገኙበትን አሰራር እንዲዘረጉ ሃሳቡን ለሥራ አመራር ኮሚቴ ያቀርባል፡፡ ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

ኘ) የስትራቴጂካዊ የተግባራት አፈፃፀም፣ የፋይናንስ ቁመና እና አስተዳደራዊ ክንውኖች ተአማኒነቱን በጠበቀ ሁኔታ በፅሁፍ ለአባላት እንዲደርስ ያደርጋል፣

o) Luulah egla wagsiisak amolladi maybalaalaqa adoytiitih aba

p) Adda lowsis aysuk akah yayse innah cato takke oytitte lowsis maroh xayyoysak abni foxooxay tambulleeh iyya alfimtuh celta qokol aba.

q) Maxxat meqe taama gabbaaquu kee faynansi maybalaalaqa taama miraacissa maroh, lowsis maroh kee wagiita doolat xagarah waktil xayyoysa

r) Eglak kulli ayroh taama tasgayye taamah exxah abbobtih tamlisan mihrat leelak, faxximtam cubbusak xayyoysa. Idnisah waqdi taamaynit xiinissoh miracsenta elle itta innal tamlisah

s) Taamah exxah abbobtih kee tamlisen mihrat leelah matteebanni dudday leh iyyat xoqoysimak ayro taamah rorsah lofti keenih bicsa agdaabe keenit kattaatah agaaradah.

2. Luulah egla ciggiila saqal exxah abbobtii kee geeri taamaynit kee mihrat leela tamlisso, liisiyyo, faxximta barittô caddo faxxiima abak raag, ken abtoo kee qaaqa, taamal sugaanah gide sahdayti caylih xiinissoo kee daddoosih miracsentak ugutak tekkek waytam diggoysa

3. Luulah eglak yontocowwe baxsa le edde cabok teneh akkewaytek taama miracisso maro adoyti, hinnay borxi adoyti hinnay taameynak xayi ramad ummaan luula taamah eglah addat ma tamlima.

ኦ) ስለ ኀብረት ሥራ ማህበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለአባላት ገለፃ ያደርጋል፣

ከ) የውስጥ ቁጥጥሩ እንዲሻሻል የሚረዱ መረጃዎችን ለቁጥጥር ኮሚቴ አባላት በማቅረብ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች መፍታት እንዲቻል ተገቢውን እገዛ ይሰጣል፡፡

ወ) ጥራቱን የጠበቀ የሥራ ሪፖርት እና የፋይናንስ መግለጫ ለሥራ አመራር ኮሚቴ፣ ለቁጥጥር ኮሚቴና አግባብ ላለው ባለስልጣን በጥራት፣ በጊዜ፣ በመጠን ያቀርባል፡፡

ዘ) የማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያንቀሳቅሱ የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ተቀጣሪ ባለሙያዎች እንደ አስፈላጊነቱ አጥንቶ ያቀርባል፣ ሲፈቀድ በሠራተኛ አስተዳደር መመሪያ መሠረት ቅጥር ይፈፅማል፡፡

ዠ) ለሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ቅጥር ባለሙያዎች ቴክኒካዊ ብቃቱን ተጠቅሞ የዕለት ተዕለት ተግባራትን መሠረት ዝርዝር የስራ ድርሻ ያወጣል፣ አፈጻጸማቸውንም በየጊዜው ይገመግማል ወይም እንዲገመገም ያደርጋል፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበሩ የምክትል ስራ አስኪያጅ፣ የክፍል ኃላፊዎች እንዲሁም ሌሎች የቅጥር ሠራተኞች ወይም ባለሙያዎች አቀጣጠር፣ ምልመላ፣ ተፈላጊ የትምህርት ዝግጅት፣ የትምህርት ደረጃ፣ ተፈላጊ የስራ ልምድ፣ ሥልጣንና ተግባራቸው እንዲሁም የሥራ ዘመናቸውን በሚወጣው የሰው ኃይል አስተዳደርና ልማት መመሪያ መሠረት መፈፀሙን ያረጋግጣል፡፡

3) በኅብረት ሥራ ማህበሩ በሰጠው ልዩ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር የሥራ አመራር ኮሚቴ ወይም ቦርድ አባል ወይም የቅጥር ሰራተኛ የቅርብ ዘመድ የሆነ ሰው በማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ውስጥ አይቀጠርም ወይም አይሾምም፣

## 69) Taamah exxah saqolti kee tamleynit tamlissoo kee xiinisso

Luulâ taamah eglalik taameynit elle tamlisan inna kee xiinisan inni luulâ taamah eglak sahdayti caylih xiinissoo kee daddoosih miracsental elle tan innal yagdubeenim akkuk ciggilta abtoo kee qaaqa alle lon

1. Tamlisen taamaynit luulâ taamah eglak matteebinnaa kee xiinisso taama aban.
2. Sissin mihrat kee caddo le tamlisen taameynit loonuh yanin xiqtoo kee ixxiga taamat qangeegissi heelon
3. Adoytit ixxi yammaguh taamitan, yaylemmen saamitte waktil akah tambaxe innah aban.
4. Adoytiitik addâ kappital sinnih adoytit gabat akah dadla innah aban
5. Qadaagah oytitte gorrisak meqennah massoysak luula eglah adoytit inkih woo xaagi akah gufa innah aban
6. Tamlisen taameynit eglak oytitte digga haak ayfaf yaceen
7. Eglak cisab qasrisak, cisab kulli ayro yayseqarren, kulli alsal alifak meqennal abbaxuk ooxit taamah bicat sugan

## 69. የሥራ ክፍል ኃላፊዎች እና ቅጥር ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር

የኅብረት ሥራ ማህበራት የቅጥር ሠራተኞች አቀጣጠርና አስተዳደር በኅብረት ሥራ ማህበሩ የሰው ኃይል አስተዳደርና ልማት መመሪያ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1) የቅጥር ሠራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበሩን ቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ስራዎች ይሰራሉ፣
2) የተለያየ ሙያና ደረጃ ያላቸው የቅጥር ሰራተኞች ያላቸውን ክህሎትና እውቀት አሟጦ መጠቀም፤
3) የአባላት ቁጥር እንዲያድግ ተግቶ መስራት፣ የተሸጡ እጣዎች በወቅቱ እንዲያልቁ መስራት፣
4) አባላት የውስጥ የካፒታል አቅም በራሳቸው በአባላት እንዲያድግ ማድረግ፣
5) የገበያ መረጃዎችን በመፈላለግና በሚገባ በማደራጀት ለኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ተደራሽ ማድረግ፣
6) የቅጥር ሰራተኞች የኅብረት ሥራ ማህበሩ መረጃ በሚገባ በመያዝ አገልግሎት መስጠት፣
7) የኅብረት ሥራ ማህበሩ በዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ በመጠቀም ሂሳብ በየእለቱ መመዝገብ፣ በየወሩ መዝጋትና በሚገባ በመያዝ ለኦዲት ዝግጁ ማድረግ፣

8. Adoytitik maddur gabat agle dadlisak xoqoysi leela ken aban
9. Ta egla kulli adoytih im kinnim aamanuk inki intit wagitak qadlik yan gital ayfaf yaceenimi
10. Luulah eglak baxaabaxsa le addah abinitte digga luk aaxaguk kee assakaxxuk taamitan
11. Luulâ taamah eglah madma, adoytit fayxi tonnaah miraacinni edde cabooba nagay axmiquk, buttiinul taamitaanama
12. Eglak taamah angagoyya wagsiisak miraacisa xagar, tagdube gabaa kee lofti leela faxxiima qokol kee cato abtuh gabbaaquu kee oyti gufsaanama.
13. Eglak gaddaa kee iko meqennal dacrisak alhumitte missah abbaxuk kee eglâ madmaak iroh geeri xoqoysit akah ase wayta innah aban
14. Adoytiitik gabat aglee kee xoqoysimiyyi lofti akah dadla innah mirocti illuk gacak maqar luk taamitaanama
15. Egla dadal kee adoytit dadal kee xoqoysimiyyi itta qeedaalak gexuh sinni qaaqak yawqeenimi
16. Luulâ taamah eglah mirocti egla ken im kinnim, daga raqta lowsiisa kinnoonum edde cabo tacayo kinnoonum keenih mihrat qokol keenim abaanama

8) ለአባላት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ፣

9) ሁሉንም አባላት ባለቤትንተ በመቀበል በእኩል በማየትና ፍትሃዊ የሆነ አገልግሎት መስጠት፣

10) የኅብረት ሥራ ህግና የተለያዩ የውስጥ አሠራሮችን ጠንቅቆ በማወቅና አክብሮ መስራት፣

11) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ዓላማ፣ የአባላትን ፍላጎት እንዲሁም የአመራሩን ውሳኔዎች በአግባቡ በመረዳትና የቡድን ስሜት ፈጥሮ መስራት፣

12) የኅብረት ሥራ ማህበሩን የሥራ እንቅስቃሴዎች በተመለከተ አመራር አካሉ፣ አስፈፃሚና ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ውሳኔ፣ ድጋፍና ዕገዛ መስጠት እንዲችሉ ሪፖርትና መረጃዎችን ተደራሽ ማድረግ፤

13) የኅብረት ሥራ ማህበራት ሃብትና ንብረትን በአግባቡ መጠበቅ፣ መረጃዎችን አደራጅቶ መያዝና ከማህበሩ ዓላማ ውጪ ለሌላ አገልግሎት እንዳይውል ማድረግ፣

14) የአባላት የተሳትፎና የተጠቃሚነት ድርሻቸው እንዲያድግ ከአመራር አከላት ጋር በመሆን ጠንክሮ መስራት፤

15) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ዕድገትና የአባላት ተጠቃሚነት ዕድገት ተጣጥሞ እንዲሄድ ሀሳፊነታቸውን መወጣት፤

16) የኅብረት ሥራ ማህበር አመራር አካላትን ባለቤትነታቸውንና የበላይ ተቆጣጣሪነታቸውንና ውሳኔ ሰጭነታቸውን ዕውቅና በመስጠት በሙያ መደገፍ፤

17. Luulâ taamah eglah taama gexse taamita marah ken taamah qaaqa keenil tabisak esserime loonum kee ken taama baxissi heeh qaduk keenil tabisak taamitaanama.

## Bacar heele exxa

## Luula taamah eglaalih xisoo kee abina yaysiiseenim kee caddo keenik baxisak qasrisaanama.

### 70) Luulâ taamah eglaalik xiso rekisso wagittaama

1. Luulâ taamah eglaali cubbusok ugutak ken dadalak, adoytit fayxik, doolat fayxi lofti leelâ fayxii kee wakti caalatak ugutak xisso rikisso fidsaanam duudaanah
2. Ummaan luulâ taamah eglah rekisso akah xissimte madmaa kee abto yagdaboonuh amolladi mododol mango xongolol faaticisenim yakkem faxximte
3. Ta miracsentak ugutak taamal asisan eglak xiso rekisso kulli caddol tan maroora taamah faxxu wayta mihrat leela addat leeh, miyyi miyyin gubat raaqam (amrih gubat raaqam) dagaak gubah hinnay gammih elle yanin inna yaybulleem faxximta
4. Luulâ taamah eglaali edde yufkunen taamah caalatak hinnay afaafayih caalatak ugutak hinnay gufeenih yanin dadal caddok ugutak xiso rekisso keenik kulli uddural wagitak yaysiiseenim

17. የኅብረት ሥራ ማህበር ሥራ አስኪያጆች ለቅጥር ሠራተኞች የሥራ የሃላፊነትና ተጠያቂነትን በግልፅ ለይቶ በመስጠት ማሰራት፤

## ክፍል ስምንት

## የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት፣ አሰራር ማሻሻል እና በደረጃ በመለየት ማዘመን

### 70. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት ድርጅታዊ መዋቅር፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት በጥናት ላይ በመመስረት ከእድገታቸው፣ ከአባላት፣ ለመንግስት፣ ከባለድርሻ አካላት ፍላጎት አንፃር እና ከጊዜው ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት መዋቅራዊ አደረጃጃታቸውን ሊዘረጉ ይችላሉ::
2) የማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር መዋቅራዊ አደረጃጀት የተቋቋመለትን ዓላማና ተግባር ለማሳካት የሚያስችልና በጠቅላላ ጉባዔ አባላት አብላጫ ድምፅ የጸደቀ መሆን ይኖርበታል::
3) መዚህ መመሪያ መሰረት ሥራ ላይ የሚውለው የኅብረት ሥራ ማህበሩ ድርጅታዊ መዋቅር በየደረጃው ያሉ ኮሚቴዎችንና ለሥራው የሚያስፈልጉ ባለሙያዎችን አጠናቅሮ የያዘ፣ የተጠሪነት እርከኖችንም ከላይ ወደ ታች ወይም ወደጎን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል::
4) የኅብረት ሥራ ማህበራት እንደሚሰማሩበት የሥራ መስክ ወይም አገልግሎት ወይም እንደየዕድገት ደረጃቸው መሰረት ድርጅታዊ መዋቅራቸውን አስፈላጊነቱ በየጊዜው እየታየ ሊያሻሽሉ ይችላሉ::

5. Luulâ taamah eglaali farmo duudusak keenik qambalsima xalot faxxiima caddol geysiisoonuh xiso rekisso keenik
    a) Kabxah ixxigaa kee xiqtok ugtan
    b) Edde yufkunen taamah faacit kee adoytit kee lofti leela fayxi fanteyna abte
    c) Mihrat moddaqiinnu kee xiqtô dudda xalootut axayuk geyan maysok ugutak
    d) Miraacisa marok miraacini doorii kee ken im kinnim diggoysak
    e) Tamlen taameynit luk xayi ikkeek angaarawuk sissik sarriimaane le xalot geysiisa
6. Luulâ taamah eglaalih rekisso hirrig axcewaytaah, rekissô wilaq eeli heeh kulli marih giniyya kee ixxigâ tabsa ilsiisam yakkem faxximta
7. Luulah eglak rekisso abtoo kee qaaqa, esserimiyya kee faaticisiyyi reeda miroctih kee taamita marah ken caddo yaceem takkem faxximta
8. Eglak rekisso, egla qaalaltaah, qaxmeqe ceelo takkuh, abtoota dudda leeh xiqto le barte caylih miraacinnul tagdubem xiqsiisam faxximte
9. Xisô rekisso tan taamah rorta faxxiima xiqto luk, taamoomi leh tan cemerraaku kee barittok loonuh gide luk tammoysak eglaalik caddo qeedalissah yan sahdayti cayla xisaanam duudaanah

5) የኅብረት ሥራ ማህበራት ተልኳቸውን በማሳካት የሚጠበቅባቸውን ሁሉ አቀፍ ውጤት በሚፈለገው ደረጃ ማሳካት እንዲችሉ መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው፤
    ሀ) የቢዝነስ እውቀትና ክህሎትን መሰረት ያደረገ፣
    ለ) የተሰማሩበትን የስራ መስክ የስራ ፍሰት እና የአባላትን እና የባለድርሻ አካላትን ፍላጎት ማዕከል ያደረገ፣
    ሐ) የሙያ ልህቀትን፣ እውቀትና ክህሎትን ከውጤት ጋር ያስተሳሰረ እና ስኬትን መሰረት ያደረገ፣
    መ) የአመራር አካላትን የመምራት ሚና እና ባለቤትነት የሚያረጋግጥ፣
    ሠ) ከቅጥር ሰራተኞች ጋር በቅርበት እየተገናኙ ፈጣንና ቀጣይነት ያለው ስኬት የሚያስመዘግብ፣
6) የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚኖራቸው አደረጃጀት ያልተንዛዛ መዋቅራዊ ሰንሰለት ኖሮት የሁሉንም አካላት ፈጠራ እና የዕውቀት ሽግግር የሚያበረታታ መሆን አለበት::
7) የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅራዊ አደረጃጀት ተግባርና ኃላፊነት፣ ተጠያቂነት እና የመወሰን ስልጣንን ለአመራር አካላትና ለቅጥር ሠራተኞች እንደአግባቡ የሚሰጥ መሆን አለበት፣
8) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ፡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ተወዳዳሪና አርአያ እንዲሆኑ ተግባሮቻቸውን ብቃትና ክህሎት ባለው የተማረ የሰው ኃይልና አመራር መምራት አለባቸው፣
9) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ያለውን የሥራ ዝርዝር ከሚፈልገው የብቃት ክህሎት፣ ከስራዎች ውስብስብነት እና ካለው የትምህርት ዝግጅት ጋር በማጣጣም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ደረጃ የሚመጥን የሰው ሃይል ማደራጀት ይችላሉ፣

10. Luulâ taamah eglaali xisok rekisso sahlisak hirigtam abak qasrisak intih tambulle agdaabee kee agdabisiyyi xiqtoh adafitte yafdigeenim faxximta.

11. Xisô rekissôh farmo yakkaqu duuda xiqtoo kee abak raage leeh niya meqe mihrat leela hirigak aysaaduk abaanam faxximta.

12. Luulâ taamah eglaali taaceh tan, investimenti, matteebannu buqrek masaaniqih baritto kee ekistenshin aydakaakan taddiiraari miraacissaah, xiinissa, tonnah sissin cubbuso abta xisoosa ginaanam faxximta.

## 71) Luulâ taamah eglaalih xissoh maysaasa wagittaama

1. Luulah eglak farmo tangaddabuh xissô maysaasa hangissam;
   a) Abtootaa kee tagdabô fanat maqar le angaaraw kee ogoysen taama ginoonu xiqsiisa xiso fidsaanama
   b) Dago sahdayti caylat xalu meqe abtoy sitta waklissa abaanam faxximta
   c) Taameynitik taama duddat xoqoysimak maxxat meqe, xaloot maqaane maqarroysa abina kattaatana
   d) Faxxiima xalot baahoonuh, rikê raqle rekissoosa inkih hinnay garab akak yaysiiseenimi

10) የኅብረት ሥራ ማህበራት መዋቅራዊ አደረጃጀታቸውን ምቹ እና ሳቢ አድርገው በማዘመን የሚታዩ የመፈፀምና የማስፈፀም የአቅም ማነቆዎችን መፍታት ይኖርበታል፣

11) መዋቅራዊ አደረጃጀቱ ተልዕኮ ሊሸከሙ የሚችሉ በቂ ችሎታ፣ ልምድ እና የሥራ ላይ ተነሳሽነት ያላቸውን ባለሙያዎች መሳብና ማቆየት የሚያስችል መሆን ይኖርበታል፣

12) ኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጧቸውን የኢንቨስትመንት፣ የሚካናይዜሽን፣ አግሮ-ኢንዱስትሪ እና የኅብረት ሥራ ኤክስቴንሽን፣ የትምህርትና ስልጠና ፕሮግራሞች የሚመሩ እና የሚያስተዳድሩ እንዲሁም የተለያዩ ጥናቶችን የሚያካሄዱ አደረጃጀቶች መፈጠር ይኖርበታል፡፡

## 71. የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት ስለማሻሻል፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩን ተልዕኮ ለማሳካት እንዲቻል የአደረጃጀት ማሻሻያው ትኩረት የሚያደርገው፤
   ሀ) በተግባራትና በፈጻሚዎች መካከል ጠንካራ ግንኙነትና ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር የሚያስችል ተቋማዊ አደረጃጀት መዘርጋት፣
   ለ) በትንሽ የሰው ኃይል ውጤታማ እና እርስ በርስ የሚመጋገቡ ተግባራትን ማከናወን የሚያስችል አሰራርን መከተል፣
   ሐ) የሰራተኞችን የስራ ክህሎት በአግባቡ በመጠቀም ጥራትና ውጤታማነትን የሚያጎለብት ዲፓርትመንትን መሰረት ያደረገ ዘዴን መጠቀም፣
   መ) የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ውስንነት ያለባቸውን ድርጅታዊ መዋቅሮች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል

2. Ummaan luulâ taamah egla fidisseh tan rekissoosah faxximta abtoo kee qaaqa baxsa luk daffeysaanam faxximta

## 72) Luulâ taamah eglaalik abini siiraat yaysiiseenim wagittaama

1. Luula taamah egla gufteh tan dadal caddok ugutak tanih tan abtootak tambulle ugxeera fokkaaqak qusba qasri abto fan yaysiiseenim faxximta.
2. Luulâ taamah eglaalih radmoo kee farmok ugutak yabbixsime xalu geysiisa tayse miracsentitte madqooqi, addax into, aysaasuk taama bagul asisaanam faxximta.
3. Qaafiyat le luulâ taamah eglaali ginoonu xiqsiisa qusba abni siiratwa cubbussol baxisak fidsaanam faxximta.
4. Taamah exxaaxi, hortaati kee taameynit sitta yaxmiqe mara akkuk, tittak barta mara akkuk sitta gablusa mara ken abta taamâ siirat fidsaanam faxximta.
5. Adoytit faxah yan investiment, matteebanni, buqrek sanaaqat kee buqreh ekistenshin ayfaf baar luk maxxat muquk elle duudusoonu xiqan taama siirat abnisaanam faxximta.

2) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ለዘረጋቸው ድርጅታዊ መዋቅሮች የሚያስፈልጉ ተግባርና ኃላፊነቶችን ለይቶ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

## 72. የኅብረት ሥራ ማህበራት የአሰራር ስርዓት ስለማሻሻል፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር ያሉ አሰራሮች ላይ የታዩ ችግሮችን በጥናት ፈትሾ በአዳዲስ ዘመናዊ አሰራሮች ማሻሻል ይኖርበታል፡፡

2) የኅብረት ሥራ ማህበራት መርህና ተልዕኮን መሰረት ያደረገ፣ ተጨባጭ ውጤትን የሚያሳካ፣ የተሻሉ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ውስጠ ደንቦች፣ ማኑዋሎችን በማሻሻል ስራ ላይ ማዋል ይኖርበታል፡፡

3) ጤናማ ኅብረት ሥራ ማህበራትን መፍጠር የሚያስችሉ አዳዲስ የአሰራር ስርዓቶችን በጥናት በመለየት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

4) የስራ ክፍሎች፣ ቡድኖች እና ሠራተኞች እርስ በርስ የሚናበቡ፣ የሚቀናጁ፣ መማማርና የጋራ ዕድገትና ተጠቃሚነትን መርህ እንዲጎለብት የሚያደረጉ የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት ይኖርበታል፤

5) አባላት የሚፈልጉትን የተለያዩ የኢንቨስትመንት፣ የሜካናይዜሽን፣ አግሮ-ኢንዱስትሪ እና የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን በስፋትና በጥራት ተደራሽ ለማድረግ የሚስፈልጉ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 73) Luulâtaamah eglaalik sahdayti gaddih xiinissoo kee daddos maysaasa wagittaama

1. Luulâ taamah eglaalih abto kabxah ixxiga luulâ taamah takkusaa kee baxsa le caalatat xakbisak tabbixe tayse barittoo kee abak raagle mihrat leelat absiisaanama.
2. Luulâ taamah eglaali loonuh yan qaawek ugutak, taameynit raagisoonuh, ilsiisoonuh cato le qaduk tan meklaa kee ilsis abina taamal asisaanam faxximta.

## 74) Luulâ taamah eglaali caddibnal baxsaanam wagittaama

1. Luulâ taamah eglaali leh tan farmoo kee aban taamoomik uguta yayse ayfaf kee hangi geyoonuh wagiita doolat xagar bicsah yan magdok ugutak caddibnal baxsiman.
2. Luulâ taamah eglaali caddibnal baxsaanamih magdok ugutak agaarad elle yakkem kulli caddibnal geytima wagiita doolat xagar xisah yan mihrat leelah ergah gaba.
3. Xissiimah yan mihrat leelah ergah adoytiitih manga, kulli makaadoh sahdaytih caylih mangal baxsa aalle le. Kinnuk too mihratat yayse ixxiga le sidiica makeelta mihrat leela edde tanim faxximta.

## 73. የኅብረት ሥራ ማህበራት የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት ስለማሻሻል፤

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ተግባር የቢዝነስ እውቀትን ከኅብረት ሥራ ጽንሰ-ሃብና ልዩ ባህሪ ጋር አጣምረው በያዙ፣ የተሻለ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ባላቸው እና ተወዳዳሪ በሆኑ ባለሙያዎች /ፕሮፌሽናልስ/ መተግበር አለበት፡፡
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት ያላቸውን አቅም መሰረት በማድረግ ሠራተኛን ለማቆየትና በስራ ላይ ለማትጋት የሚያግዝ ግልፅ የክፍያ እና የማበረታቻ አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## 74. የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ መለየት

1) የኅብረት ሥራ ማህበራት ባላቸው ተልዕኮ እና በሚያከናውኑት ተግባራት መሰረት የተሻለ አገልግሎት እና ትኩረት ማግኘት እንዲችል አግባብ ያላው ባለስልጣን በሚያዘጋጀው መስፈርት መሰረት በደረጃ ይለያሉ፡፡
2) የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ የመለያ መስፈርት መሰረት ግምገማ የሚካሄደው በየደረጃው ባለው አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚያቋቁሟቸው የባለሙያዎች ቡድን አማካይነት ይሆናል፡፡
3) የሚቋቋመው የባለሙያዎች ቡድን እንደየአደራጅ ተቋሙ የሰው ኃይል ብዛት የሚለያይ ሆኖ በሙያው የተሻለ ክህሎት ያላቸው ሦስት መዞኝ ባለሙያዎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

4. Bicsan caddibna baxsih magdooda, kulli luulah eglah qaynat kee caddibnal baxsa luk, ta magdooda kulli waqdi yaysiiseenih.
5. Ken qamalak ugutak makeelo magdooda kulli yaysiiseenih wagiita doolat xagarah xayyoysak makeelo magdo yaysiiseenim xiqaanah.
6. Ta maasayyak 74(5) madqeenim elle anuk bicsen caddibna baxsih magdok abnissol tumbullee foxo cubbussot baxisak kulli 3 liggidal akah yaysiisen innah abelon.
7. Bicseenih yanin luulah eglaalih makeeloh magdok, makeeltah tan mihrat leela axmaq geyoonuh aydakaakan keenih antocowwele.
8. Ummaan luulah egla makeelaanam bajet liggidi gaba kalla heeh ooxit keenik abeenik sarra.
9. Inki luulah egla makeelimmi itteh caddibna teetih yeceenik geera ciggiilta makeeloh makeelimam naharsi makeeloh xalu teetih yeceenih 3 liggidaak geera.

## 75) Luulâ taamah eglaalih caddibnaa kee caddibna baxsih magdooda

1. Luulâ taamah eglaalih caddibnah baxsih magdooda ciggiltam teeti muxxi hangi akah yaceenim.

4) የሚዘጋጁት በደረጃ የመለያ መስፈርቶች እንደየኅብረት ሥራ ማህበራት፡ አይነትና ደረጃ የሚለያይ ሆኖ መስፈርቶቹ በየጊዜው የሚሻሻሉ ይሆናል፡፡

5) በባህሪአቸው በተቀመጠው የመመዘኛ መስፈርት ለመመዘን አስቸጋሪ የሚሆኑ የኅብረት ሥራ ማህበራት ካጋጠሙ መመዘኛ መስፈርቱ ለሚመለከተው አካል በማቅረብ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተዘጋጀው የኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃ መለያ መስፈርት አተገባበር ላይ የታዩ ክፍተቶችን በጥናት በመለየት በየሦስት ዓመቱ እንደአስፈላጊነቱ እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

7) በተዘጋጀው የኅብረት ሥራ ማህበራት መመዘኛ መስፈርት ላይ ለሚመለከታቸው መዛኝ ባለሙያዎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

8) ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር የሚመዘነው የበጀት ዓመቱ ተጠናቆ ኦዲት ከተደረገ በኋል ይሆናል፡፡

9) አንድ የኅብረት ሥራ ማህበር ተመዝኖ ደረጃ ከተሰጠው በኋላ በቀጣይ የሚመዘነው የመጀመሪያው የምዘና ውጤት ከተሰጠ ከሦስት ዓመት በኋላ ይሆናል፡፡

## 75. የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃዎች እና የደረጃ መለያ መስፈርቶች

1) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ለመለየት የተመረጡ ደረጃ መለያ መስፈርቶች ትኩረት የሚደርገው በዋናነት፤

a) Luulah eglak qadaaga gabat agle
b) Yayfoofen adoytiitih manga
c) Taama farakka
d) Murtit qagsan nihiri
e) Buqrê matteebannih xayyoosu
f) Maali ayfaafih gudduumiyya
g) Barte caylay taama miraacisah maallo
h) Ayyuntiino gabat agle
i) Tirfi keefo elle tan inna
j) Qasriino le cisab abbaxa
k) Kappital dadalak loonumu
l) Geeri taamah celta abtoota

2. Luulah eglaali caddibna daffeysaanam akah faxximteemik sababittek garab
   a) Ken elle daffeysen caddibnal ken ceela qokol kee kattat keenih aboonu
   b) Ken caddol arqo gino keenit takku
   c) Ken caddibnal lowsis keenit yakku
   d) Mablaa kee farmo sinnik arac xagsoonuh baxsa le gurral ken catoonu
   e) Luulah eglaali qokolta arqo ginaa kee lofti leela taaceeh tan qokol kee ayfaafay sissikih awqenta dagoysaa kee gudduume yakke gidi.
3. Luulâ taamah eglaali caddibna baxsih magdol agaaradda ken heenih geyaanah yanin muuxal caddibna keenik baxsimelle.
4. Ta maasayyak 75(1)(a-j) daffeysen caddibnâ baxsih magdok ugutak agaaradan luulah egla geytem caddibna "A" hinnay "B" hinnay "C" akkele. Takkay immay kulli caddibna kulli waqdi aysiisuk akah gexan innah hangi acayuk cattiiman.

ሀ) የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብይት ተሳትፎ፣
ለ) የሚያገለግሏቸው አባላት ብዛት፣
ሐ) የሥራ ስፋት፣
መ) በምርት ላይ እሴት መጨመር፣
ሠ) የግብርና ቴክኖሎጂዎች አቅርቦት፣
ረ) የፋይናንስ አገልግሎት ተደራሽነት፣
ሰ) በተማረ የሰው ኃይል ተግባሮቻቸውን የመምራት፣
ሸ) የማህበራዊ ተሳትፎ፣
ቀ) የትርፍ ክፍፍል፣
በ) ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ፣
ተ) ባላቸው የካፒታል ዕድገት፣
ቸ) ሌሎች ተያያዥ ተግባራት፣

2) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ማስቀመጥ ካስፈለጉባቸው ምክንያቶች መካከል የሚጠቀሱት፤

ሀ) የተለዩበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ ደረጃቸውን የሚመጥን ድጋፍና ክትትል ለማድረግ፣
ለ) ደረጃቸውን የገናዘበ አቅም ግንባታ አገልግሎት ለመስጠት፣
ሐ) አቅማቸውን ያገናዘበ ቁጥጥር ለማድረግ፣
መ) ራዕይና ተልዕኳቸውን እንዲያሳኩ በተለየ መልኩ ለማገዝ፣

ሠ) ኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚደግፉ አቅም ገንቢዎች እና ባለድርሻ አካላት የሚሰጧቸው ድጋፍ እና አገልገሎት ቀልጣፋ፣ ወጭ ቆጣቢ እና ተደራሽ እንዲሆን በማስፈለጉ ነው፡፡

3) የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት ተገምግመው በሚያገኙት ውጤት መሠረት ደረጃቸው የሚለይ ይሆናል፡፡

4) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 75 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ-ተ) ላይ በተቀመጠው በደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት የሚገመገም ማንኛውም ኅብረት ሥራ ማህበር የሚያገኘው ደረጃ "ሀ" ወይም ደረጃ "ለ" ወይም ደረጃ "ሐ" ይሆናል፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ ደረጃ በየጊዜው እያተሻሻለ እንዲሄድ ትኩረት ተሰጥቶ የሚደገፍ ይሆናል፡፡

5. Baxsiyyi magdol agaaradda heenih "C" akah yeceen luulah egla"B" fanah gexak teneek "A" fan akah korta innah qokol kee kattat keenit akkele.
6. Tonna ceelak caddibnak "B" rankisen luulah egla fooca fan abtah tan angagoyyal kee keenit aban qokolut "A" caddibna guftuh qokol kee kattat teetit yakke.
7. "A" caddibnal tan luulah eglaali tayse taamoomi abak giffo le agdaabeh addat culoonuh hangi acayuk taama akkele.

## 76) Luula taamah eglaalik caddibnaani maybalaalaqa wagittaama

1. Daffeysen caddibnâ baxsih magdok ugutak amolladi muuxi %80 gabaa kee wohuuk daga takke ximmooma geyte eglaalih yaceenim "A" caddibna.
2. Ta maasayyak 71(1) madqimtem elle anuk amolladi muuxi keenik %55--%79.99 gaba gufte eglaalih yaceenim "B" caddibna kinnuk %25--%54.99 gaba yakke muuxa bahte eglaalih yaceenim "C" caddibna.
3. "A" caddibnal baxsenimih addak %90 gaba muuxak bahte eglaalik meexen abak raaq keenik beetak geeri luulah eglaalit akah tabsan innah aban.

5) በመለያ መስፈርቱ ተገምግመው በደረጃ "ሐ" ላይ የተለዩ የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃቸውን ከ "ሐ" ወደ "ለ" እና በሂደትም ወደ "ሀ" ለማሻሻል ድጋፍና ክትትል ይደረግላቸዋል፤

6) በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ "ለ" ላይ የሚመደቡ የኅብረት ሥራ ማህበራት በቀጣይ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እና በሚደረግላቸው ድጋፍ ወደ ደረጃ "ሀ" እንዲያድጉ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

7) በ "ሀ" ደረጃ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት የተሻለ ተግባር በመፈጸም የላቀ አፈፃፀም ውስጥ መግባት እንዲችሉ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል፡፡

## 76. ስለኅብረት ሥራ ማህበራት የደረጃዎች መግለጫ

1) በተቀመጠው የደረጃ መለያ መስፈርት መሰረት ያገኙት ጠቅላላ ውጤታቸው 80 ከመቶ እና ከዚያ በላይ የሆነ ነጥብ ላገኙ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጥ ደረጃ "ሀ" ነው፡፡

2) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 71 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ጠቅላላ ውጤታቸው ከ55---79.99 ከመቶ የሆነ ነጥብ ላገኙት የሚሰጥ ደረጃ "ለ" ሲሆን ጠቅላላ ውጤታቸው ከ 25---54.99 ከመቶ የሆነ ነጥብ ላገኙት የኅብረት ሥራ ማህበራት ደረጃ "ሐ" የሚሰጣቸው ይሆናል፡፡

3) በደረጃ "ሀ" ከተለዩት ውስጥ ከ90 ከመቶ በላይ ያመጡ የኅብረት ሥራ ማህበራት ምርጥ ተሞክሮዎችን በመቀመር ወደ ሌሎች ኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሰፋ የሚደረግ ይሆናል፡፡

4. "B" caddibnal baxsen eglaalik muuxi %70–%55 gabak addah geyte luulâ taamah eglaalik hunuun ugxe keenik baxisak baxsa le cato keenit akkele

5. "C" caddabnal baxsen eglaalik %55 gabak addah muuxa bahte eglaali aggiriqqe sinni qokol kee kattat keenit akkele.

6. Ta maasayyak 76(5) madqimtem elle anuk %25 gaba yakke muuxa bahte eglaali, luulâ taamah eglaalih raaqaanam bice waytanamih taagah wagiita doolat xagar madqak ugutaak yacee edde cabok ugutak ken aggilee kee geeri marat ken xakbe yakke.

7. Daffeysen magdok ugutak geyaanah yanin muuxi %95 gabak daga akak gufte egla, geeri marak baxsimak foocah gexxeemih taagah (outlier) foocah taxco iyya migaq keenih yantocoowe.

8. Agdaabel daffeyte makeeloh inkinkinnak daga tekke eglaalih qokol abak mango gaddaa kee wakti keenit baysaanam hinnay sinni xiqak akah soolan innah abaanama.

## 77) Luulâ taamah eglaalik caddibna baxissa tagdubuse maroh xiso wagittaama

1. Luulâ taamah eglaalik caddibna baxsoonuh 5 adoyta le tagdubuse maro xissiimele.

4) በደረጃ "ለ" ከተለዩ ውስጥ ውጤታቸው ከ70 እስከ 55 በመቶ በታች ያመጡት የኅብረት ሥራ ማህበራት ውጤታማ እንዲሆኑ መሰረታዊ ችግራቸውን በመለየት ልዩ ድጋፍ ይሰጣቸዋል፡፡

5) በደረጃ "ሐ" ከተለዩ ውስጥ ከ55 በመቶ በታች ውጤት ላስመዘገቡ ቀጣይነት ያለው ድጋፍና ክትትል በማድረግ እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

6) በዚህ አንቀጽአንቀጽ 76 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከ25 ከመቶ ነጥብ በታች የሚያገኙ የኅብረት ሥራ ማህበር ሆነው ሊቀጥሉ ስለማይችሉ አግባብ ያለው ባለስልጣን በሚወስነው መሰረት ሕጉን ተከትሎ እንዲፈርሱ ወይም እንዲወሃዱ ይደረጋል፡፡

7) በተቀመጠው የደረጃዎች መለያ መስፈርት መሰረት በሚያገኙት ውጤት ከ95 ከመቶ ባላይ የሚያገኙ ኅብረት ሥራ ማህበራት ከሌሎች ተለይተው ወደጫፉ የወጡ (outlier) ተብለው ይለያሉ፡፡

8) በአፈፃፀማቸው ከተቀመጠው የመመዘኛ ስታንደርድ በላይ የሆኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ድጋፍ ለመስጠት የበለጠ ሀብትና ጊዜ ማባከን ሳያስፈልግ ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## 77. የኅብረት ሥራ ማህበራት በደረጃ የሚለይ አስተማባሪ ኮሚቴ ስለማደራጀት፣

1) የኅብረት ሥራ ማህበራትን በደረጃ ለመለየት አምስት አባላት ያሉት አስተማባሪ ኮሚቴዎች ይቋቋማሉ፣